በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን
ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት
ክፍል

# የሀዋሪያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለአንብቦ መረዳት ክሂል ያለው አስተዋጾ (በአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ

ክብነሽ ታደሰ

አማካሪ

ደረጀ ገብሬ

ሐምሌ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የሀዋሪያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለአንብቦ መረዳት ክሂል ያለው አስተዋጾ (በአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ክብነሽ ታደሰ

ሐምሌ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ጆርናሊዝምና

ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር

ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

የሀዋሪያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የአንብቦ መረዳት

ችሎታን ለማዳበር ያለው አስተዋጾ በአራተኛ ክፍል

ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ነው

የማስተር ዲግሪ ማሟያ ጥናት

የፈታኞች ቦርድ አባላት

አማካሪ ፡- ደረጀ ገብሬ ፊርማ ---------------- ቀን ------------

ፈታኝ ፡- ---------------- ፊርማ -------------- ቀን -----------

ፈታኝ ፡- ---------------- ፊርማ -------------- ቀን -------------

# ምስጋና

ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ስሰራ በቅድሚያ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ለረዳኝ ፈጣሪዬ ምስጋና ይገባዋል ።

የገነንዘብ ገድጋፍ በማድረግ እየረዳ ላስተማረኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም እውቀታችሁን ሳትሰስቱ ስለችኝ ደከመኝ ሳትሉ እውቀት እየመገባችሁ ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ያበቃችሁኝ የእውቀት አባቶቼ መምህራን ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ከፍ ካለ አክብሮት ጋር ነው።

ይህ ፅሁፍ ለስኬት እንዲበቃ አማካሪዬ አቶ ደረጀ ገብሬ ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠትና ስህተቴን በማረም፣ ለስራዬ መሳካት ፈጣን ምላሽ በመስጠትና በመምራት፣ ጥናቱ ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲይዝ ላደረጉልኝ እገዛ ምስጋናዬ ከፍ ካለ አክብሮት ጋር ነው።

የሃሳብ ድጋፍ በማድረጋና ለስራዬ መሳካት ላልተለዩኝ ባለቤቴ ማረጌ እምሩና ልጆቼ ህሊና ማረጌ ሳምራዊት ማረጌ፣ ልደት ሙሉጌታ፣ ማህሌት አስፋው ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

በጥናቱ ሂደት ወቅት ለልምምድ ተማሪዎችን በመምረጥ፣ ተማሪዎቹ በጥናት ተሳታፊ እንዲሆኑ በማበረታታት፣ እስከ መጨረሻው ትብብራቸው ላልተለየኝ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በመምረጥ ቅድመ ትምህርት ፈተናና ድህረ ትምህርት ፈተና በመገምገም ፣ በማስተካከል ፈተናዎችን፣ በማረምና ስዕል በመሳል ሙያዊ ድጋፋቸው ላልተለየኝ የአማርኛ ትምህርት ክፍልና ሌሎችም መምህራን ይሄይስ ፀጋዬ ፣ ነፃነት ከበደ፣ ፋንታነሽ በላይ ፣ ዘላለም አድማሱ፣ ቀርመሪዮስ ደርሶ ፣ መታሰቢያ ዳንኤል፣ አስቴር ካሳሁንና፣ ሙሉነሽ ውብሸት ላደረጋችሁልኝ ድጋፍ ከልብ አመሰግናለሁ ።

ጥናቱን እንዳካሂድና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ለፈቀዱልኝ ለሀዋሪያው ጴጥሮስ ርዕሰ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም በማማከርና ልዩ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለመምሀር አናንያ ደርሶ እና አለምነሽ ሮበሌ ምስጋናዬ ከላቀ አክብሮት ጋር ነው ።

# ማውጫ

ማውጫ ገፅ

ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ v
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1. መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4
1.3 የጥናቱ አላማ ........ 5
1.3.1 የጥናቱ ዋና አላማ ........ 5
1.3.2 ዝርዝር አላማዎች ........ 5
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 5
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 6
1.6 የጥናቱ ውሱንነት ........ 6
ምዕራፍ ሁለት ........ 7
2. የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ........ 7
2.1. አንብቦ መረዳት ........ 7
2.2 የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ........ 7
2.3 የማንበብ ክሂልን የማዳበሪያ ደጋፊ ተግባሮች ........ 8
2.4. የትምህርት መርጃ መሳሪያ ምንነት ........ 9
2.5. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ለምን እንጠቀማለን? ........ 9
2.6. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አመራረጥ ........ 10
2.7. ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ጥቅም ........ 11
2.8. የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ........ 12
2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት ........ 12
ምዕራፍ ሶስት ........ 15

3. የአጠናን ዘዴ ........................................ 15
3.1. የጥናቱ ንድፍ ........................................ 15
3.2. የመረጃ ምንጭ ........................................ 15
3.3. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........................................ 16
3.3.1. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........................................ 16
3.3.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........................................ 16
3.3.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........................................ 17
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................................ 18
3.4.1. ፈተና ........................................ 18
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................ 20
4.የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ ........................................ 21
4.1. የመረጃ ትንተና ........................................ 21
4.1.1.የቅድመ ፈተና ውጤት ትንተና ........................................ 21
4.1.2.የድህረ ፈተና ውጤት ትንተና ........................................ 24
4.1.2.1.የአንብቦ መረዳት እውቀት መመዘኛ የድህረ ፈተና ጥያቄዎች ውጤት ትንተና ........................................ 24
4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........................................ 31
ምዕራፍ አምስት ........................................ 33
5. የጥናቱ ማጠቃለያ፣መደምደሚያ እና አስተያየት ........................................ 33
5.1. የጥናቱ ማጠቃለያ ........................................ 33
5.2. የጥናቱ መደምደሚያ ........................................ 35
5.3. አስተያየት ........................................ 36
ዋቢ መጽሐፍ ........................................ 37
አባሪዎች ........................................ 40
አባሪ ሀ-ሰ ........................................ 40

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ1፡ቅድመ ትምህርት ፈተና የተማሪዎች ቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ ................ 22
ሰንጠረዥ 2፡- ቅድመ ትምህርት ፈተና የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት የባእድ ናሙናዎች ቲ- ቴስት ........................................................................ 23
ሰንጠረዥ 3፡- ድህረ ትምህርት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝርዝር ንዑሳን ክሂል ጥያቄዎች ቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ ..................................................................... 25
ሰንጠረዥ 4፡-ድህረ ትምህርት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝርዝር ንዑሳን ክሂል ጥያቄዎች ውጤት የባእድ ናሙናዎች ቲ- ቴስት ......................................................... 26
ሰንጠረዥ 5፡- ድህረ ትምህርት የተማሪዎች ጥቅል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጥያቄዎች.. 28
ሰጠረዥ 6 ፡-ድህረ ትምህርት የተማሪዎች ጥቅል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጥያቄዎች ውጤት የባእድ ናሙናዎች ቲ- ቴስት ......................................................................... 29

# አጠቃሎ

ጥናቱ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በወረዳ ስድስት የሀዋሪያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓመተ ምህረት በመማር ላይ ባሉ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው ። የጥናቱ አላማ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለአንብቦ መረዳት ክሂል ያለው አስተዋፆ በሙከራዊ የምርምር ዘዴ ለመፈተሽ ነው ። ጥናቱ ከመከናወኑ በፊት ካሉት ሶስት ክፍሎች በቀላል እጣ ናሙና አመራረጥ ስልት የሁለት ክፍል 96 ተማሪዎች ተመርጠዋል ። ጥናቱ ሁለት ቡድኖች የያዘ ሲሆን እነሱም የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ናቸው ። በሁለቱ ቡድኖች መካከል የችሎታ ተመጣጣኝነት መኖሩ አለመኖሩን ለመለካት ሲባል ምንባቡ ከተለያዩ ዕሁፎች በመውሰድና በመምረጥ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል። በቅድመ ትምህርት ፈተና በተገኘው የቲ -ቴስት ውጤት እንደሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት59.47ሲሆን ልይይቱ ደግሞ 0.12500 ነው ። የሙከራው ቡድኑ አማካኝ ውጤት 59.35 ሲሆን ልይይቱ ደግሞ 0.12500 ነው ። የሁለቱንም ቡድኖች አማካኝ ውጤትና ልይይት ግምት ውስጥ በማስገባት በቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የችሎታ ተመጣጣኝነት እንዳለ ለመረዳት ተችሏል ። ቀጥሎም የሙከራ ቡድኑን በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመታገዝ አንብቦ መረዳትን ሲማሩ ፣ የቁጥጥር ቡድኑ ቀደም ያለትምህርት መርጃ መሳሪያ አንብቦ መረዳትን ተምረዋል። ሁለቱም ቡድኖች ለሰባት ተከታታይ ሳምንታት ለ14 ቀናት ከተማሩ በኋላ ለሁለቱም ቡድኖች ድህረ ትምህርት ፈተና ተዘጋጅቶ እንዲፈተኑ ተደረጓል ።የድህረ ትምህርት ፈተና የቲ -ቴስት ውጤት እንደሚያሳየን የሙከራ / የተጠኚ / ቡድኑ አማካኝ ውጤት 82.3958 ሲሆን ልይይት ደግሞ 7.06426 ነው ። የቁጥጥር አማካኝ የቲ -ቴስት ውጤት 66.4583 ሲሆን ልይይቱ ደግሞ 12.18642 ነው ። የሁለቱ ቡድኖች አመካይ ውጤት የሚያሳየን ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ እንደሚያሳድግ ወይም እንደሚያጎለብት ነው። መረጃዎቹም መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በደምዳሜያዊ ስታስቲክስ የቲ -ቴስት ተተንትኗል ። በዚህ መሰረት ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዳግም ልኪት ያሳድጋል /ያጎለብታል/ ፤ እንዲሁም የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ለማዳበርና የተሻለ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል ። በጥናቱ ግኝት መሰረት ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት መሻሻል መፍትሄ የሚሆኑ ሀሳቦች ተሰንዝሯል። ከመፍትሔ ሀሳቦቹም ለመምህራን፣ የመማሪያ መፅሐፍት አዘጋጆች፣ ለመርሃ ትምህርት አዘጋጆችና ጥናት አድራጊዎች አራቱን የቋንቋ ክሂሎች አቀናጅቶ ከማስተማር አኳያ በስፋት ቢጠናና ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልትን በመተግበር አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማዳበር ተማሪዎች ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ እርስ በእርስ መረጃ እንዲለዋወጡ በማድረግ፣ ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉና እገዛ እንደሚያስፈልጋቸው እና ትምህርቱ ሲዘጋጅ በስዕላዊ መርጃ መሳሪያ ቢዘጋጅ ተማሪዎች ውጤታማ እንደሚሆኑ ይህ ጥናት አስገንዝቧል።

# ምዕራፍ አንድ

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን ለመግባቢያነት የሚጠቀሙት የሰው ልጆች ብቻ ናቸው። ስለሆነም ሰዎች እርስ በርስ ለመግባባት ይህንን ቋንቋ ሲጠቀሙና የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑበት ይታያል። በመሆኑም በመግባባት ውስጥ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በማቀናጀት ይጠቀሙባቸውል። እነዚህም የቋንቋ ክሂሎች ማዳመጥ ፣ መናገር ፣ ማንበብና መፃፍ ናቸው ።

ማንበብ ከአራቱ ክሂሎች መካከል ዋና እና አስፈላጊ ክሂል ነው። የንባብ ልምድ በዋናነት የሚዳብረው በትምህርት ቤት ነው። የማንበብ ክሂል አፈፈቱም ሆነ ኢአፈፈቱ በትምህርት ቤት የሚያገኙት ክሂል ነው። የማንበብ ክሂል እንደማዳመጥ ሁሉ የመቀበያ ክሂል ነው። ንባብን ለተለያዩ ተግባራት እንገለገልበታለን። ንባብ ለፅህፈት የሚሆኑ ግብአቶች መቅሰሚያ፣የምናነበው የፅሁፎችን መልዕክት የመረዳት ችሎታ ማዳበሪያ፣ ከአነበብነው ነገር አንድ የምንፈልገውን ነገር ለማወቅ ነው ።

ደረጀ ገብሬ (2013፣10) እንደጠቀሱት ትምህርት የሚጀምረው ንባብ ሲጀመር ነው። ከፊደል እውቀት ተነስቶ በየደረጃው እየሰፋና እየጠለቀ ሲሄድ ትምህርት ተከናወነ እንላለን። ይህ ወደ እውቀት ያሸጋግራል ። በመረጃ ላይ የተመረኮዘ ግንዛቤ በመረዳት ይገኛል። ከእውቀት ደግሞ ወደ ማንጠርና ፍሬ ከገለባ ወደ መለየት ይደርሳል። ፍሬን ከገለባ የለየ ሰው ደግሞ በንባቡ ከገፋ ወደመጠንቀቅ (ኃላፊነትን ወደ መወጣት፣ አሳምሮ፣ አስተባብሮ ወደ መስራት) ይራመዳል። ጠንቅቆና አሳምሮ የሚሰራ ደግሞ የነገሮችን (የሀሳቦችን) ልክና ደረጃ ለይቶና አውቆ በአይነት በአይነቱ ማደላደል፣ ማመቻቸት ይችላል ሲሉ አብራርተዋል።

ተስፋዬ (1981) በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ በመረዳት በኩል መሰረታዊ ችግር እንዳለ ይጠቁማሉ። በአብዛኛው የአማርኛ ቋንቋን አንብቦ መረዳት በኩል ያለው ትልቁ ችግር ተማሪው ያነበበውን ነገር ተረድቶ እውነታውን እንደሚፈልገው አይነት ተስማሚ መሆኑን አመዛዝኖ መቀበሉ ወይንም አለመቀበሉ ቀርቶ ገና ለግንዛቤ የሚያበቃ ክሂል ያልዳበረ እንደሆነ በፅሁፋቸው ላይ ጠቁመዋል። ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ከመምህራኖች ይጠበቃል። የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳርያዎች ተጠቅመው በማስተማር ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ማዳበር ይቻላል። በማንኛውም ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት የታቀደውን አላማ ከግብ ለማድረስ

ተማሪዎች በእያንዳንዱ የቋንቋ ክሂል ብቃት አግኝተው ታላሚውን ቋንቋ ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡ ትምህርቱን ግልፅና ቀላል አድርጎ ለማቅረብ ጉልበትና ጊዜን ቆጥቦ ለማስተማር የትምህርት መርጃ መሳርያን መጠቀምን ይጠይቃል፡፡

እንደ ደረጀ (2013፣89) የማንበብ ክሂልን ማዳበሪያ ተግባሮች ብለው ከጠቀሷቸው ውስጥ አንዱ ስዕላዊ ልቦለዶች፣ የኮምክና መፃህፍት (comic book) እና የካርቱን ፅሁፎች ያሉባቸው መጻሕፍት ማቅረብ ልጆች ለመፅሀፍ ያላቸውን ፍቅር ለማጎልበት አንዱ መንገድ ሊሆን ይችላል:: የኮምክና መጻሕፍት ወተስፋዬ (1981) በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ በመረዳት በኩል መሰረታዊ ችግር እንዳለ ይጠቁማሉ፡፡ በአብዛኛው የአማርኛ ቋንቋን አንብቦ መረዳት በኩል ያለው ትልቁ ችግር ተማሪው ያነበበውን ነገር ተረድቶ እውነታውን እንደሚፈልገው አይነት ተስማሚ መሆኑን አመዛዝኖ መቀበሉ ወይንም አለመቀበሉ ቀርቶ ገና ለግንዛቤ የሚያበቃ ክሂል ያልዳበረ እንደሆነ በፅሁፋቸው ላይ ጠቁመዋል፡፡ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ከመምህራኖች ይጠበቃል፡፡ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳርያዎች ተጠቅመው በማስተማር ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ማዳበር ይቻላል፡፡ በማንኛውም ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት የታቀደውን አላማ ከግብ ለማድረስ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የቋንቋ ክሂል ብቃት አግኝተው ታላሚውን ቋንቋ ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡ ትምህርቱን ግልፅና ቀላል አድርጎ ለማቅረብ ጉልበትና ጊዜን ቆጥቦ ለማስተማር የትምህርት መርጃ መሳርያን መጠቀምን ይጠይቃል፡፡

ይም ስዕላዊ ልቦለዶች የሚባሉት በመጠናቸውም ሆነ በቋንቋ አጠቃቀማቸው በእጅጉ ቀለል ያሉ ናቸው፤ በየመፅሐፍቱ ውስጥ የሚቀርበውም ይዘት ደረጃ በደረጃ ተለጣጥቀው በሚቀርቡ ስዕሎችና አጫጭር ምልልሶች ታጅበው የሚዋቀሩ ናቸው ፡፡ በቃላት ክብደት፣ አዲስነት ወይም በአረፍተነገር ቅንብር ውስብስብነት የተነሳ አንብቦ ለመረዳት አዳጋች የሚሆኑ መፅሐፍትን ለመረዳት ስዕሎችንና አጫጭር መገለጫዎች እጅጉን ጠቃሚዎች መሆናቸውን ባለሙያዎች ያስረዳሉ:: መምህራን ይህን ተረድተው የተማሪዎች ግላዊ የንባብ ፍላጎት ይጨምር ዘንድ ይህንንም በማድረግ ልዩ ልዩ ማስተማሪያ መሳሪያዎችንና ያቀራረብ ብልሃቶችን መጠቀም ያስፈልጋቸዋል፡፡

ከላይ ከተገለጸው ሐሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች ውስብስብ ነገሮችን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ እና ግልፅ እንዲሆንላቸው መምህራን በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መጠቀም እንዳለባቸው እና መምህራንም ስለ ስዕላዊ ትምህርት መርጃ መሳሪያ

ያላቸውን እውቀት እና ችሎታ የተሸለ እንዲሆን እና ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው በመርጃ መሳሪያ ለመጠቀም የአጠቃቀም ግንዛቤ እንደሚያስፈልግ ይገልፃል

ዚነት (2003) Aggarwal (1996) ጠቅሳ ቋንቋን ስናስተምር በቀላሉ መግባባት እንዲቻል በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በመታገዝ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ከረቂቅና ውስብስብነት ወደ ተጨባጭና ግልፅነት አቅልሎ በማቅረብ ነው ። ለተማሪዎች የሚቀርበው ትምህርት በቀላሉ ግልፅ እንዲሆንላቸው የትምህርት መርጃ መሳሪያን መጠቀም ትምህርቱን ቀላልና ግልፅ ያደርጋል ። እዚህ ላይ ስለ ትምህርት መርጃ መሳሪያ ሲነሳ መምህራን ስለ ትምህርት መርጃ መሳሪያ ያላቸው እውቀትና አመለካከት ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ እንደሆነ (Bestet፡ 2000) ይገልፃል ። በቋንቋ ትምህርት ስዕላዊ መርጃ መሳሪያን መጠቀም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን እንገነዘባለን ።የመማር ማስተማር ሂደቱን ግልፅና ተጨባጭ ለማድረግ ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሳሪያ መምረጥ ያስፈልጋል ።

በተጨማሪም እኚሁ አጠኚ(2003) MC Arthur (1989) Harmer (2001) ጠቅሰው የትምህርት መርጃ መሳሪያ አስፈላጊነትና ጥቅሙን ሲያብራሩ የተነደፉትን ይዘቶች ለመተግበር እና በተማሪዎችና በሚማሩት ይዘት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ግልፅና ተጨባጭ ለማድረግ የትምህርት አሰጣጡን ሳቢና ማራኪ ለማድረግ የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን መጠቀም ያስፈልጋል። የትምህርት መርጃ መሳሪያ አስፈላጊነትን ለተግባራዊ ልምምድ ብሎም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት ያገለግላል። ይህ ማለት የትምህርት መርጃ መሳሪያ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከማነሳሳትም ባሻገር የተማሩትን ትምህርት አይረሴ እንዲሆን ያደርጋል። በተጨማሪም Harmer እንደተናገረው ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ግልፅና ተጨባጭ እንዲሆን በስዕላዊ መርጃ መሳሪያ መጠቀም የቋንቋ ትምህርት መረጃ መሳሪያዎች የቋንቋውን ትምህርት ስፋትና ጥልቀት እንዲረዳው ያደረርጋል ። በአጠቃላይ ቋንቋ የማስተማር ተግባር በስዕላዊ መርጃ መሳሪያ ቢታገዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው ።

ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው የአንብቦ መረዳት ችሎታን በውጤታማ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ አሰራሮች ያሉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አንዱ ስእላዊ የትምህርት መርጃ መሳርያን ተጠቅሞ ማስተማር ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ ከማድረግ ባሻገር የተማሪዎችን ፍላጎት በማነሳሳት ትምህርቱ ቀላልና ግልፅ ሊሆን እንደሚችል ነው ።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር በማንኛውም የትምህርት መስክ ውጤታማ እንዲኮን በስዕላዊ የትምህህርት መርጃ መሳሪያ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ያስፈልጋል ፡፡

የኔሰው (1990) Dymock (2005) ጠቅሰው እንደገለጹት ሁልጊዜ እንደምንመለከተው ተማሪዎች ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሳያዳብሩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ይጨርሳሉ፡፡ ስለሆም የብዙ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡

ለአንብቦ መረዳትም ሆነ ለትምህርት ጥራት መውደቅ ብዙ ምክንያቶች ሲኖሩ ከእነሱ ውስጥ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከክፍል መቅረት፣የተማሪው በፈተና ውጤት ዝቅተኛ መሆን፣በክፍል ውስጥ የደጋሚዎች ቁጥር መጨመር፣የተማሪዎች መጠነ ማቋረጥ መጨመር፣ ወዘተ ናቸው፡፡

ቀጥሎም ለዚህ መፍትሔ ሊሆኑ ከሚችሉት አንዱ Amare (1998፣ 282) የትምህርት መርጃ መሳሪያን በመጠቀም ማስተማር ነው ይላሉ፡፡ መምህሩ ያለ ትምህርት መርጃ መሳሪያ ተማሪዎችን ሳያሳትፍ በገለፃ ብቻ በማስተማርና በሰሌዳ ላይ ፅፎ ተማሪዎች እንዲገለብጡ ከማድረግ በተጨባጭ በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች መርጃ መሳሪያዎችን አዘጋጅቶ ማስተማር ችግሩን ያቃልላል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ የምንረዳው ለትምህርት ጥራት መዳከም የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉና በቋንቋ የትምህርት መርጃ መሳሪያ መጠቀም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

አጥኚዋ በአዲስ አበባ መስተዳድር ሀዋርያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ባስተማረችባቸው አመታት ከመምህራን ጋር ባደረገቻቸው የእርስ በርስ የልምድ ልውውጥ በምታይበት ጊዜ ተማሪዎች የተፃፈውን የአንብቦ መረዳት ቀርቶ ቃላት አገጣጥሞ ቃል መስርቶ ለማንበብ ሲቸገሩ በማየቷ ነው ፡፡ ምናልባት ይህንን ችግር በስዕላዊ መርጃ መሳሪያ ተጠቅሞ ማስተማር ችግሩን ሊፈታው ይችላል ፤ ከሚል እሳቤ ይህን ጥናት ልታጠና ተነስታለች ፡፡

በተጨማሪም እስካሁን በተደረገው ክለሳ መሰረት በዚህ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች በተቀራራቢነት ቢኖሩም ምናልባት ይህንን ችግር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማጥናት የሚታየውን ችግር ይቀርፈው ይሆን? የሚለውን ጥያቄ በአዕምሮዋ አጭሯል፡፡ ስለሆነም አጥኚዋ በምታስተምርበት ትምህርት ቤት አንብቦ መረዳት ለማስተማር በሚደረግ ሂደት

በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ተጠቅሞ የአንብቦ መረዳትን ለማስተማር አስተዋፅኦ ይኖረው ይሆን? የሚለውን በጥናት ለመፈተሽ ካላት ፍላጎት የተነሳ ነው ፡፡ ስለዚህ አጥኝዋ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር አነሳሽነት አለው ይሆን? የሚሉ መልስ የሚሹ ጥያቄዎች አንስታለች ፡፡ እነሱም ፦

1. ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ተጠቅሞ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ምን አስተዋፅኦ እንዳለው ለመዳሰስ ይቻል ይሆን?
2. ያለስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ማስተማርና አንበቦ መረዳትን ለማስተማር ምን ተፅዕኖ ይኖረዋል? የተፅዕኖው መጠን ምን ያህል እንድሆነ ለመለየት ይቻል ይሆን?
3. ተማሪዎች በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የአንብቦ መረዳትን ከተማሩ በኋላ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን ማዳበሩን መለየት ይቻል ይሆን?

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሀዋሪያው ጸጥሮስ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ማስተማር የአንበቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ነው ፡፡

### 1.3.2 ዝርዝር አላማዎች

ጥናቱ ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ያስችላል ፡፡

1 ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ተጠቅሞ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ምን አስተዋፅኦ አለው?
2 ያለስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ አንበቦ መረዳትን ማስተማር ምን ተፅዕኖ ይኖረዋል? የተፅዕኖው መጠን ምን ያህል ነው?
3 ተማሪዎች በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ከተማሩ በኋላ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን ለማሻሻል ይችሉ ይሆን?

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል ፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳትን ችሎታን ሲያስተምሩ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም እንዲረዱእና ትኩረት እንዲሰጡ የሚያመላክት መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ ።
- ለቋንቋ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል አማራጭ መንገድ ስለሚጠቁም ።
- የአንብቦ መረዳት ችሎታን በስላዊ መርጃ መሳሪያ ተጠቅመውና ያለመርጃ መሳሪያ ማስተማር መካከል ያለውን ልዩነት በመገንዘብ በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ አስወግዶ ሌሎች መምህራን በስዕላዊ መርጃ መሳሪያ መማር ማስተማር ያለውን ጥቅም እንዲረዱ ያደርጋቸዋል ።
- የቋንቋ መምህራን ስለ ትምህርት አሰጣጣቸው የተሸለ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ተማሪዎቻቸውን የበለጠ እንዲረዱ ያደርጋል (ይጥቁማል) ።
- ለወደፊት የመማሪያ መፅሀፍ ለሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ስዕላዊ መረጃ መሳሪያዎችን በሚያዘጋጁት መፅሀፍት ውስጥ አካተው እንዲያዘጋጁ ይረዳል ።
- በተመሳሳይ ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ ተመራማሪዎች እንደመነሻና ማጠቀሻ ሆነው ያገለግላሉ ።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ተጠቅሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማዳበር ያለው አስተዋፅኦ ላይ ያተኩራል። ጥናቱ የሚመለከተው የአራተኛ ኤ እና ቢ ክፍል የአማርኛ ተማሪዎችን ብቻ ነው። ጥናቱም የሚከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍል ከተማ ወረዳ 06 በሀዋሪያው ጰጥሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው።

## 1.6 የጥናቱ ውሱንነት

በዚህ ጥናት ውስጥ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመጠቀም የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ተደርጓል። ጥናቱ ውስን የሚሆንባቸው ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም ሊጠቀሱ ከሚችሉት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ቲ - ቴስት ለመስራት የእውቀት ውስንነት ታይቷል።

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

## 2.1. አንብቦ መረዳት

Davis (2011) Ontario (2003) እና Tankersly (2005) እንደሚገልፁት አንብቦ መረዳት በተለጣጣቂነት የሚደረግ ልምምድ ደረጃ በደረጃ በሂደት እየዳበረ የሚሄድ ክሂል ነው፡፡ በጥቂት ጊዜ የሚጎለብት ሳይሆን በተከታታይ በሚደረግ ያላሰለሰ ልምምድ ሳቢያ በአእምሮ ውስጥ የሚከናወን እድገት ነው፡፡ ተማሪዎች ደጋግመው አንብበው ሲረዱ በህይወት ቆይታቸው የቀደመ እውቀታቸውንና አረዳዳቸውን እያሳደጉ ይመጣሉ፡፡

Johnson (2008) የአንብቦ መረዳት ክሂል ቋሚ መሰረቱ መረዳት ነው፡፡ አንባቢው ለማንበብ የቀረበን ፅሁፍ ከቀደመ እውቀቱ ጋር በማቀናጀትና በመለማመድ ለፅሁፍ ትርጉም መስጠት መቻል ነው፡፡ የማንበብ ችሎታ በፅሁፍ ውስጥ ያለን አንድ ንዑስ ሃሳብ ከሌላው ሀሳብ ጋር የማቀናጀት ተግባር ነው፡፡ በፅሁፍ ውስጥ ያሉ መልዕክቶችን ትርጉም ባለው መልኩ ማቀናበር መቻል አንዱ አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ ገልጿል፡፡

የኔሰው Brown (1994) Wallace (1992) ጠቅሶ አንብቦ መረዳት ማለት አንድ ሰው አንድን ምንባብ ከአነበበ በኋላ የፅሁፉን መልዕክት መገንዘብ ወይም መረዳት መቻል ማለት ነው፡፡ የአንብቦ መረዳት ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ አንድን ምንባብ የሚያነቡ የተለያዩ ሰዎች አንድ አይነት አረዳድ አይኖራቸውም፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ሰዎች ከምንባብ በፊት ያላቸው ቅድመ ምንባብ እውቀት አንድ አይነት ባለመሆኑ ነው ፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው አንብቦ መረዳት ማለት ተፈላጊ የሆነውን መረጃ ለመምረጥ አስፈላጊውን ማስፈር መቻል ነው ፡፡ አንባቢው ተፈላጊ ነገሮችን ብቻ በመለየት እንዴት ማንበብ እንዳለበት ካወቀ በአንብቦ መረዳት ረገድ ችግር አይገጥመውም ፡፡

## 2.2. የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች

የአንብቦ መረዳት ክሂል በውስጡ በርካታ ክሂሎችን ያቅፋል ፡፡ ይህ የቋንቋ ፊደል ቅርጽ መለየት፣ ሆሄያትን አገጣጥሞ ቃላት መመስረትን ፣ቃላትን አገጣጥሞ ሐረጋትን ማንበብ ፣ ሐየረጋትን አገጣጥሞ አረፍተነገር መመስረትን ፣ የቃላትን ፍቺ ማወቅ ፣በግልፅ የሰፈረን መረጃን አንብቦ መረዳትን፣ አዳዲስ ቃላትን ከምንባቡ አውዳዊ ፍቺዎች ማውጣትን ፣ፅንሰ ሀሳባዊ ትርጉምን መገንዘብን ፣በአረፍተ ነገር መካከል የሚኖረውን ዝምድና መለየትና መረዳትን ፣ጠቃሚ ነጥቦችንና ጠቃሚ ያልሆኑትን ነጥቦች ለይቶ መውጣትን ፣የምንባብን

ዋና ሀሳብና ዝርዝር ሐሳብን መውጣት ፣የምንባብን ሐሳብ ጨምቆ መውጣት፣ አረፍተነገርን በቅደም ተከተል ማስተካከልና መፃፍ ፣ስርዓተ ነጥብ፣ ቃላት በማጥበቅና በማላላት ፍቺን ማወቅ ፣የመሳሰሉትን ክሂሎች ይይዛል።

## 2.3. የማንበብ ክሂልን የማዳበሪያ ደጋፊ ተግባሮች

ደረጀ (2013፣89-90) ልጆች በራሳቸው ፍላጎትና በግላቸው መፅሐፍ አንስተው ለማንበብ ሊሞክሩ ይችላሉ። ይሁንና ከባድ ሆኖ ካገኙትና ካልገባቸው ተስፋ ሊቆርጡና መንፈሳቸውም ሊዳከም ይችላል። መፅሀፍ መርጦ ለማንበብ መሞከር በጎ ተግባር ቢሆንም፣ ተፈላጊ ውጤት እንዲገኝ ለተማሪዎች ደረጃ የሚመጥነውን መምህሩ ለይቶ ሊያመላክት ይገባል። መምህሩ ሊያተኩርባቸው ከሚገቡ የመምረጫ ስልቶች ውስጥ፣

- የኩምክና መፅሀፍት ስዕላዊ ልቦለዶች፣ የኩምክና መፃህፍት (Comic Books) እና የካርቱን ፅሁፎች ያሉባቸው መጻህፍት ማቅረብ ልጆች ለመጻህፍት ያላቸውን ፍቅር ለማጎልበት አንዱ መንገድ ሊሆን ይችላል። የኩምክና መጻህፍት ወይም ሥዕላዊ ልቦለዶች የሚባሉት በመጠተናቸውም ሆነ በቋንቋ አጠቃቀማቸው በእጅጉ ቀለል ያሉ ናቸው። በየመፃህፍቱ ውስጥ የሚቀርበው ይዘት ደረጃ በደረጃና ተለጣጥቀው በሚቀርቡም ስዕሎችና አጫጭር ምልልሶች ታጅበው የሚዋቀሩ ናቸው። ይህም አቀራረባቸው በኩምክና መፃኅፍት ውስጥም ሆነ በስዕላዊ ልቦለዶች የሚቀርቡ ምስሎች አማካይነት የትረካዎቹ ሂደት የተሳካ ይሆናል። በቃላት ክብደት፣ አዲስነት ወይም በአረፍተ ነገር ቅንብር ውስብስብነት የተነሳ ለአንብቦ ለመረዳት አዳጋች የሚሆኑ መፃህፍትን ለመረዳት ስዕሎችንና አጫጭር መግለጫዎች እጅጉን ጠቃሚ መሆናቸውን ባለሙያዎች ያስረዳሉ። መምህራን ይህንኑ ተረድተው የተማሪዎች ግላዊ ፍላጎት ይጨምር ዘንድ መጠቀም ይኖርባቸዋል።
- በልዩ ልዩ ስዕሎች የታጀቡ ልቦለዶች፣ አብዛኛውን ጊዜ ለልጆች የሚቀርቡ መፃህፍት በስዕል የታጀቡ ናቸው። ለልጆች ወይም ለወጣቶች የሚቀርቡ ብቻ ሳይሆኑ ለጎልማሶች የሚሰናዱ የልቦለድ ስራዎችም በስዕል ታጅበው ይቀርባሉ። ለምሳሌ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም፣ አደፍርስ፣ አርአያ፣ አግአዚ፣ እንደወጣች ቀረችና የመሳሰሉትን መፃህፍት መጥቀስ ይቻላል፤ እነዚህ መፅሀፍት ሲነበቡ ስዕሎቻው ምን ያህል ድጋፍ ያደርጉልን እንደ ነበረ ያነበብናቸው እናስታውሳለን። ለልጆች ተብለው የሚመረጡ ልቦለዶች ግጥሞች ተውኔቶች በስዕል የታጀቡ ቢሆኑ

ልጆች ለመፃህፍት ያላቸውን ፍቅር በመጨመር ረገድ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ መቻላቸውን ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ፡፡

## 2.4. የትምህርት መርጃ መሳሪያ ምንነት

Heinich et al (1996) ስለትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ምንነት እንደሚከተለው ይበይናሉ፡፡ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ትምህርት ነክ ጉዳዮችን ከተለያዩ ምንጮች እንዲያዙ የሚያግዙና ትምህርታዊ ዕቅዶችን እውን የሚያደርጉ መሳሪያዎች ወይም ቁስ አካላት ናቸው፡፡

አሰፉ Nkuuhe (200:224) ጠቅሰው የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የሚለው ፅንሰ ሀሳብ በብዙ የተለያየ ምክንያቶች የተነሳ በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡፡ በየትኛውም ደረጃ በሁሉም የትምህርት አይነትና የትምህርት መስኮች በመምህራንና በተማሪዎች ዘንድ ለመማር ማስተማር ሂደት የሚውሉትን ፅንሰ ሐሳቦች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ እኚህ ምሁር አያይዘው የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ሲባል የትምህርት ውጤቶችን፣ ምስሎችን፣ ሞዴሎችን፣ እውነተኛ ነገሮችን (realobjects)፣ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችንና የተለያዩ ሰሌዳዎችን በአጠቃላይ ለመማር ማስተማር ሂደት አጠቃላይና ዝርዝር የትምህርት አላማዎችን ከግብ ለማድረስና የትምህርት ይዘቶችን በተጨባጭ ለማብራራት አገልግሎት ላይ የሚውሉ የትምህርት አጋዥ መሳሪያዎች (devices) መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

የእነዚህ ምሁራን ሃሳብ ጠቅለል አድርገን ስናየው የትምህርት መርጃ መሳሪያ የሚቀርበውን ትምህርት ግልጽ፣ ተጨባጭ፣ ማራኪ፣ ትርጉም ሰጪ፣ ውጤታማ እና ዘላቂ ለማድረግ የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን፣ እውነተኛ ነገሮችንና እነሱን የሚወክሉ ተጨባጭ አምሳያዎቻቸውን ያቀፉ የመማር ማስተማር አካል ናቸው፡፡

## 2.5. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ለምን እንጠቀማለን?

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በቃላዊ ትርጉም ብቻ ቢገለፁ ለመረዳት እጅግ አስቸጋሪ የሚሆኑትን የትምህርት ይዘቶች እንደተገቢነታቸው በመወከል ተማሪዎች የመማር ልምዶችን በቀላሉ እንዲያከማቹና እንዲያሳድጉ የሚያደርጉ፣ መምህራንም ውስብስብ የሆኑ ንድፈ ሀሳባዊ የትምህርት ይዘቶችን በእርግጠኝነት እውነተኛ በሆነ መልኩ እንዲያቀርቡ የሚረዳቸው መሆኑን (Quist 2000) ያስረዳሉ፡፡

Kochare (1985:134) "ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የተደገፈ ትምህርት ሲማሩ ትምህርቱ አይረሴነትን የተላበሰ ተጨባጭነት ያለውና ተወዳጅነት እንዲኖረው ያደርጋሉ" በማለት ይገልፃሉ፡፡

አሰፉ Harmer (2001:134) ጠቅሰው ሲገልፁ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳትና ለተግባራዊ ልምምድ እንደሚያገለግሉ ይገልፃሉ፡፡ከዚህ ጋር በማያያዝ Nkuuhu (2000:226) የትምህርት መርጃ መሳሪያን የጎላ ጠቀሜታ ሲገልፁ ከስነ ትምህርታዊ ስነ ልቦና Educational Psychology ያያይዙታል፡፡ ይኸውም እያንዳንዱ ሰው የሚማረው በስሜት ህዋሳቱ በመታገዝ መረጃዎችን በመሰብሰብ እንደሆነ ያብራራሉ፡፤ ይህንኑ እኘው ምሁር ሲዘረዝሩት የትምህርት መርጃቸ መሳሪያን ስንጠቀም የተማሪዎችን ትኩረት በመሳብ፣ የመማር ፍላጎትን ያነሳሳል፣ ቡድናዊም ሆነ ግላዊ የመማር ልምድ ተነሳሽነትን ያጎለብታል፣ ተማሪዎችን በዋና ዋና የትምህርት ይዘቶች ወይም ቁልፍ ሀሳቦች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያስችላል፣የተማሪዎችንም ወይም የመምህራንን አዳዲስ የፈጠራ ችሎታ ያሳድጋሉ፣ አንድ ሂደት በእርግጠኘነት እንዲታይ ያደርጋሉ፣ ለአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ፍለጋ የሚባክነውን ጊዜ ይቆጥባሉ፣ ንድፈ ሐሳቦችን እንዲረዱ ያደርጋል፣የድርጊት ቅደም ተከተላዊ ሒደት በተማሪዎች አዕምሮ ምናባዊ ምስል በመፍጠር እየተደጋገመ እንዲመጣ ያደርጋሉ ፡፡

በተጨማሪም ረቂቅ የሆኑ የትምህርት ይዘቶችን እርግጠኛ አድርጎ በማቅረብ ተማሪዎች ያለምንም ችግር የትምህርት ይዘቶችን እንዲረዱና የማስታወስ ችሎታቸውን በማፋጠን አካባያቸውን እንዲረዱና እንዲያደንቁ በማገዝ ተማሪዎች የተለያዩ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ፣ የመገጣጠምና የመፍታት፣ችግርን ተረድቶ አብሮ የመስራት፣ችግርን የመፍታትና መፍትሔ የማፈላለግ ልምዶችን እንዲያዳብሩና የመማር ተነሳሽነትንት ለመፍጠር መምህራን የሚያቀርቧቸውን የትምህረት ይዘቶች ለተማሪዎች ተዓማኒ (እውነተኛ)፣ ተገቢና ትርጉም ሰጪ እንዲሆኑ ያስችላሉ፡፡ አሰፉ (Malawi, institute of education 2003) በመጥቀስ ያብራራሉ ፡፡

## 2.6. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አመራረጥ

መምህራን የመማር ማስተማር ተግባራትን ከመጀመራቸው በፊት የትምህርት መርጃ መሳሪያ በትምህርት ዕቅድ ውስጥ መካተት እንዳለበትና በሚያስተምሩበት ወቅትም በዕቅዱ መሰረት መገልገል እንዳለባቸው በበርካታ ጥናቶች የተደገፈና የሚታመንበት ነው፡፡ (Bowen 1982፣52) መምህራን ማጤን ያለባቸውን ነጥቦች ይዘረዝራሉ፡፡

1 የዕለቱ ትምህርት አላማና የመርሃ ትምህርቱን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዝ፣
2 ዝርዝር የትምህርት አላማ የሚያሳካ መሆኑ፣
3 በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ልዩ ልዩ ባህሪ (ዕድሜ፣ትምህርታዊ ደራና ቋንቋውን ለመማር የሚፈልጉበትን ምክንያቶች ከግምት ማስገባት መቻሉ)

መምህራን ንባብን ከማስተማራቸው በፊት ፅሁፎችን በጥንቃቄ መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ተገቢ ንባብ ለመምረጥ በቅድሚያ የንባብ መምረጫ መስፈርቶችን ማወቅ ተገቢነት ስላለው አንድ ንባብ ሊያሟላ የሚገባው መመዘኛ ብዙ ነው፡፡ ከመመዘኛው መካከል የሚመረጠው ንባብ በካርታ፣ በግራፍ በሰንጠረዥና በስዕላዊ መገለጫዎች ቢደገፍ ለተማሪዎች ተገቢ፣ ጠቃሚና ቀላል እንዲሆን የጎላ ጠቀሜታ አለው፡፡ በጥንቃቄ የተመረጠ ፅሁፍ ደግሞ በተገቢው መንገድ የተላለፈውን መረጃ በቀላሉ ለመውሰድ ያስችላል፡፡ (Nuttll 1982:25)

## 2.7. ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ጥቅም

Wright (1989፣136) እንደሚገልጹት ስዕሎች የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ለማዳበር ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ከቃላት የሚመጡት ፍቺዎች በስዕሎች ውስጥ በሚገኙ አውዳዊ አገባብ ይወስናሉ፡፡ ስዕሎች የተለያዩ አውዶችን በመፍጠር በክፍል ውስጥ ለማስተማር ላቅ ያለ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ጥቅም አስመልክተው Bowen (1982:Iv) መማር ውስብስብ ሂደት እንደሆነ በመጠቆም፣ ይህ ውስብስብ ሂደት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መጠቀም ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት እንደሚያነሳሳ ይገልፃሉ፡፡ በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማስተማር የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚጨምር ብቻ ሳይሆን የትምህርቱን ይዘት በግልፅ፣በቀላልና በተጨባጭ መልኩ እንዲረዱት እንደሚያግዛቸው፤ በቃላዊ ትምህርት ላይ ብቻ የሚያተኩረውን የመምህሩን የንግግር ጊዜ በመቀነስ የተማሪዎችን ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋሉ፤ በሚታዩ ምስሎች አማካኝነት ከክፍል ውጪ ባሉ ውጫዊ ዓለም ተጨባጭ ነገሮች ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩ ጥቅም አላቸው በማለት ያብራራሉ፡፡ የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመረዳት ስለሚያስችል ለትርጉም ፍለጋ የሚባክነውን ጊዜ ይቆጥባሉ፡ የአንድን ድርጊት ወይም ነገር ቅደም ተከተላዊ ሂደት በተማሪዎች አዕምሮ ምናባዊ ምስል በመፍጠር ሀሳቡ በምናባቸው እየተደጋገመ እንዲመጣ ያደርጋሉ፡፡ (Nkuuhe, 2000:22)

Nunan (1991:136) ስዕላዊ መገለጫዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪውን ስሜትና ፍላጎት ከመቀስቀስ ባሻገር የቋንቋ መድብለ ቃላትና ሐረጋት ዓረፍተ ነገሮችን ከመመስረት አንፃር ጥሩ ልምድ ለማድረግ እንደሚያስችሉ ይገልፃል፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው የአንብቦ መረዳት ችሎታን በውጤታማ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ አሰራሮች ያሉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አንዱ ስእላዊ የትምህርት መርጃ መሳርያን ተጠቅሞ ማስተማር ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ ከማድረግ ባሻገር የተማሪዎችን ፍላጎት በማነሳሳት ትምህርቱ ቀላልና ግልፅ ሊሆን እንደሚችል ነው ፡፡

## 2.8. የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

የሚታዩ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ተማሪዎች በንባብ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት የሚረዱበት ነው፡፡ Nuttal (1982፣ 25) የሚታዩ የትምርት መሳሪያዎች አስደግፎ ማስተማር በመካከለኛ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች የቃላት ፍቺ ግልፅ እንዲሆንላቸው እየተመለከቱ ትምህርት መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡ Aggarwal (1995:304) የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የሚላቸው፡፡ ጥቁር ሰሌዳ፣ የማስታወቂያ ሰሌዳ፣ ቻርቶች፣ ስዕሎች፣ ግራፎች፣ የቃላት ካርዶች፣ መፅሐፍት፣ ካርታዎች እና ሌሎች የማይንቀሳቀሱ ፊልሞች፣ ከርቶኖች፣ ሞዴሎች፣ ፖስተሮችና ፎቶግራፎች ናቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡

አሰፉ Bowen (1982:13-14) ጠቅሰው የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ከአገልግሎታቸው እና ከባህሪያቸው በመነሳት በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመድቧቸዋል፡፡ እነሱም፡- ስዕሎች፣ ሰሌዳዎች፣ፕሮጀክተሮች በማለት ከፋፍለው በውስጣቸውም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እንደሚያካትቱ ይገልፃሉ፡፡ እንደ Bowen ምደባ መሰረት ስዕሎች በሚለው ምደባ ስር የግድግዳ ላይ ስዕሎች እና ቻርቶች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ የቃላት ፍላሽ ካርዶች፣ የስዕል ፍላሽ ካርዶች፣ የስራ ካርዶችና የስራ ወረቀቶችን ያካትታል፡፡ ሰሌዳዎች ተብለው የተመደቡት ደግሞ ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሰራ ሰሌዳ፣ የጠመኔ ሰሌዳ፣ ነጭ ሰሌዳ፣ የማሳያ ሰሌዳ፣ የማስታወቂያ ሰሌዳና መግነጢሳዊ ሰሌዳ ሲሆኑ በፕሮጀክተሮች የሚመደቡት የአናት የአናት በላይ ፕሮጀክተር (overhead projecter)፣ ስላይድ ፕሮጀክተሮችንና ሌሎች ፕሮጀክተሮችን ያጠቃልላል፡፡

የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በየትኛውም የትምህርት እርከን ለሚሰጥ የትምህርት አይነት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ቢሆንም በተለይ አፍ መፍቻንም ሆነ ሁለተኛን ቋንቋ በማስተማር ረገድ ያላቸው ፋይዳ በእጅጉ የጎላ ነው፡፡ ስዕላዊ መግለጫዎች ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ የተማሪን ተነሳሽነት ከማጠናከራቸው ባሻገር የቋንቋውን መድብለ ቃላት እውቀትን በማስፋት በቃላቱ ሀረጋትና አረፍተ ነገርን ከመመስረት አንፃር ጥሩ ልምምድ ለማድረግ እንደሚያስችል ይገልፃሉ፡፡

## 2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ጥናቶች ለማየት ተችሏል፡፡ የኔሰው (1990) «በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቢዊ የንባብ ክሂል ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋፅኦ »በሚል ርዕስ ያካሄዱት የጥናት አላማ አማርኛ ቋንቋን ኢ-አፍፈት ተማሪዎች

በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያስችላቸውን የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል በሙከራዊ የምርምር ዘዴ ለመፈተሽ አልሞ የተነሳ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ፈተናን በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመ ሲሆን ለቁጥጥር ቡድኑ በጥንታዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የክፍል ውስጥ ክንውን በተደገፈ ልምምድ ከተደረገ በኋላ ፈተና ተሰጥቷቸው በጥናታቸው ውጤት እንደገለፁት ተጠኚ ቡድኑን በተራክቢዊ ሞዴል በመማሩ የተሻለ ውጤት እንዳሳየ ገልጿል፡፡

የየኔሰው ፅሁፍ ከዚህ ፅሁፍ ጋር የሚያመሳስለው የመረጃ መሰብሰቢያው መሳሪያ ፈተና መሆኑና በአንብቦ መረዳት ላይ የተሰራ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ሲመሳሰል፤ ይህ ጥናት በስዕላዊ መርጃ መሳሪያ መጠቀምና በአፈፊት ተማሪዎች ላይ በመስራቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ጌታቸው ኮቹ (2000) “በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የማስተማር ሒደት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም በሚል ርዕስ የተጠና ነው፡፡” ጥናቱ የሚያተኩረው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችን በማስተማር ሒደት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን የመምህራን አዘገጃጀትና አጠቃቀም የሚል ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ አንብቦ መረዳት፻ ያለው አስተዋፅኦ በመሆኑ በጥናት አካባቢ፣ በትምህርት እርከኑና አማርኛን በአፈ ፊት ለሚማሩ ተማሪዎች በመሆኑት ላይ ማተኮሩ አጠናን ዘዴውን ልዩ ያደርገዋል፡፡

ጌታቸው ለገሰ (1992) “በአዲስ አበባ መስተዳድር ለሰባተኛ ክፍል የሚተላለፍ አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት ለማሻሻል ሊያበረክተው የሚችለው አስተዋጽኦ” በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በሚደመጡ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በሬዲዮ ላይ የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ አንብቦ መረዳት ያለው አስተዋጽኦ በሚል የተሰራ ሲሆን በአላማው፣ በክፍል ደረጃው፣ በአጠናን ዘዴው፣ በሙከራዊ ወይም ፍትነታዊ የተጠና በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለፁ ድርሳናት የኔሰው ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በአንብቡ መረዳት በሙከራዊ ወይም በፍትነታዊ አጠናን ዘዴ የሰራ መሆኑ እና መረጃ መሰብሰቢያውም ፈተናና የፅሁፍ መጠይቅ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የጌታቸው ኮቼና የጌታቸው ለገሰ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው የትምህርት መርጃ መሳሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም የመምህራን አስተዋፅኦ ሲሆን ከዚህ ጥናት ልዩ የሚያደርጋቸው ይህ ጥናት ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለአንብቦ መረዳት ያለውን አስተዋፅኦ

መመርመርና ያጠናን ዘዴው በሙከራዊ ወይም ፍትነታዊ የአጠናን ዘዴ መከተሉ ልዩነት አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት ሁሉም ድርሳናት የትምህርት መርጃመሳሪያን አጠቃቀም መጥቀሳቸውና የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎቸውን መፈተሽ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል ፡፡ ይህ ጥናት ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለአንብቦ መረዳት ያለው ጠቀሜታን ስላልዳሰሱት ይህን ክፍተት ለመሸፈን የተካሄደ ጥናት በመሆኑ ጥናቱን አዲስና ልዩ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም በጊዜም ሆነ በቦታ፣በዘመን እንዲሁም በክፍል ደረጃ ጥናቶቹ ልዩነት አሳይቷል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# 3. የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽዎ በሙከራ መፈተሽ ነው። ይህ ጥናት የተከተለው የአጠናን ዘዴ ሙከራዊ ወይም ፍትነታዊ /Experimntal/ የምርምር ስልት ነው። ይህም በስታትስቲካዊ ትንታኔ በመታገዝ በተግባር የተደገፈ ምርምር የሚካሄድበት መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመከተል ነው። ሙከራዊ ምርምር የተካሄደው ሙከራ ለማድረግ አመቺ በሆነ በአብዛኛው በተመራማሪዋ በተመረጠ ቦታ ላይ ነው። ዘዴው ምንግዜም ሁለት ተለዋዋጮች ይኖሩታል። እነሱም ነፃ ተለዋዋጭና ጥገኛ ተለዋዋጭ ናቸው። ነፃ ተለዋዋጭ ተመራማሪው ሊያጠናው የፈለገው እንደአመቺነቱ የሚለዋውጠው የሚያሻሽለውና በጥገኛ ተለዋዋጭ ላይ አንዳች ውጤት ሊያመጣ ይችል እንደሆነ ምርምር የሚካሄድበት ነው። ጥገኛ ተለዋዋጭ ደግሞ በነፃ ተለዋዋጭ መለዋወጥ የተነሳ የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ነው። (ያለው፣ 2009)

በአጥኝዋ ለተገግባራዊነቱ የሁለት ቡድኖች የቅድመ ትምርትና የድህረ ትምህርት ፈተና የአጠናን ዘዴ በስራ ላይ ውሏል። የዚህ የአጠናን ዘዴ ፅንሰ ሀሳብ ሁለት ተጠኚ ቡድኖች ማለትም የሙከራውና የቁጥጥር ቡድኑ ከሙከራው አስቀድሞ ተመሳሳይ ፈተና ወስደዋል። ሁለቱም በወሰዱት ፈተና የሚያሳዩት ተመሳሳይ የችሎታ ደረጃ ምን ላይ እንደሚገኝ ታይቷል።

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን አስተዋፅኦ መርምሮ የተገኘውን ውጤት በመጠናዊ የመርጃ መተንተኛ የሚገለፅ ነው።

## 3.2. የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች በአዲስ አበባ በንፋስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምርት ቤት ውስጥ በወረዳ ስድስት የሚገኘው የሐዋሪያው ጴጥሮስ ትምህርት ቤት በ2015ዓ.ም በመማር ላይ የሚገኙ የ4ኛ ኤ እና ቢ ክፍል ተጠኚ ተማሪዎች ናቸው።

ከተማሪዎች በዋናነት የሚፈለጉት መረጃዎች ከአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በአስፈላጊው ቅደም ተከተል ተዘርዝረው በገላጭ ስልት ትንተና ተሰጥቶበታል።

## 3.3. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በንፋስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ካሉት 31 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሐዋሪያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በአላማ ተኮር አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል ። ይህን የናሙና ዘዴ መጠቀም ይተፈለገው ተመራማሪዋ ይዚሁ ትምህረት ቤት መምህርት በመሆኑዋ ጥናቱን ለማካሄድ ጊዜ፣ ወጪን፣ ጉልበትን ከመቀነስ በተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይረዳል በማለት ነው።ለጥናቱ የሚያስፈልጋት ክፍለ ጊዜ ከመደበኛው የትምህርት ሰዓት ውጪ በማጠናከሪያ ትምህርት በሚሰጥበት የትምህርት ቤቱን አስተዳደር በማስፈቀድ ተባብረዋት ነው። በዚህም የቁጥጥር ቡድኑ በሳምንት ሁለት ቀን የሙከራውንም ቡድን በሳምንት ሁለት ቀን በሁለት ክፍለ ጊዜ በማስተማር ነው።

### 3.3.1. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ አጥኚዋ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህርትነት ለረጅም ዓመታት ስታገለግል መቆየቷ ቀደም ሲል ተገልጿል። በዚህም ምክንያት የአንደኛ ደረጃ ዕርከን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግርን በቅርበት ታውቃለች። በመሆኑም የክፍል ደረጃን ከአንደኛ እስከ አራተኛ ካሉት ክፍሎች መካከል በቀላል እጣ የናሙና ስልት በመጠቀም ተመርጧል። አጥኚዋ ይህን መስፈርት አድርጋ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎችን በቀላል እጣ ናሙና መርጣ የተገበረችው ነው።

ከጥናቱ አላማ አንፃር ተተኳሪ ተጠኚዎቹ በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ተጠቅሞ አንብቦ መረዳትን በክፍል ውስጥ ለመተግበር በዚህ የክፍል ደረጃ ለመፈተሽ ህፃናት ስለሆኑ ስዕላዊ የትምህርት መርጃን መጠቀም የትምህርት ፍቅርና ተነሳሽነት እንዲያድርባቸውና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለማሻሻል ይችላል ተብሎ በመታሰቡ ነው።

### 3.3.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በሀዋሪያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚማሩ ሲሆን በጥናቱ የተካተቱት በ2015ዓ.ም በአራተኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙት 144 ተማሪዎች ሲሆኑ በዚህ የክፍል ደረጃ በሶስት ክፍሎች ተመድበዋል። ሁሉንም ተማሪዎች ተሳታፊ ለማድረግ ስለማይቻል ሶስቱን ክፍሎች በቀላል እጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በመምረጥ ነው ።በዚህም በእድል ሰጪ እጣ ናሙና ዘዴ የአራተኛ ኤ ክፍል 48 እና 4ኛ ቢ ክፍል 48 ተማሪዎች በእጣ የተመረጡ ናቸው። በመሆኑ የትምህርት ቤቱ ሙሉ ፍቃደኝነት ተጠይቆ ጥናቱ ተካሂዷል።

### 3.3.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የመምህራን የናሙና አመራረጥ ስልት መምህራን ለጥናቱ በቂ መረጃ ለማግኘት ካሉት ዘጠኝ አማርኛ ቋንቋ መምህራን 5 ዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ 4ቱ የዲፕሎማ መምህራን ናቸው።ከዲግሪ መምህራኖቹ ውስጥ ሁለቱ አራተኛ ክፍል አማርኛ የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው። ከሁለቱ መምህራን በቀላል እጣ ናሙና ስልት አንዷ መምህርት ለጥናቱ ተመርጣለች።

**የማስተማሪያ መሳሪያ**

የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን የማስተማሪያ ምንባቦች የሚዘጋጁበት ከቋንቋ ትምህርት መርሃ ትምህርት አላማዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ይዘቶች በቅድሚያ ለትምህርት ቀርበዋል። በአጥኝዋ የተዘጋጁት የማስተማሪያ ምንባቦች መልመጃዎች እና ፈተናዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች ተገቢነት የይዘት የቅርፅና የአቀራረብ ቅደም ተከተል በሚከተለው ሁኔታ ተቀምጧል። በአጥኝዋ ለማስተማሪያነት የተመረጡ ምንባቦች ከጋ'ዜጣ ፣ከመጽሐፍት፣ከመማሪያ መጸሐፍትና ከተረት መጸሐፍት የተዘጋጁ ናቸው። እንሱም የሚከተሉት ሲሆኑ ከነዚህ ምንባቦች ውስጥ ሁለቱ ለቅድመ እና ለድህረ ትምህርት ፈተና ተመርጠዋል።

ሀ. ወላጆችን ማክበር

ለ. የአሸንዳ ጭፈራ

ሐ. የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ

መ. የፕላስቲክ ተፅዕኖ

ሠ. በድሉና ውቢቱ ኢትዮጵያ

ረ. የጥንካሬ ተምሳሌ

ሸ. የስራ ክፍፍል

እነዚህ ምንባቦች ተዘጋጅተው ለሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ ፈተና ተሰቷል። ለቅድመ ፈተና ‹‹ ወላጆችን ማክበር ›› የሚለው ተመርጧል። ለድህረ ፈተናው ‹‹ የአሸንዳ ጭፈራ ›› የሚለው ምንባብ ቀርቧል። የምንባቡ አመራረጥ Wallace (1992) በሚከተለው ሁኔታ ባስቀመጣቸው መለኪያዎች ነው።

ሀ. ምንባቡ አዲስ ቃላትና የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ስርዓት የሚያስተምሩ ከሆነ ፣

ለ. ምንባቡ መሰረታዊ የአነባበብ ስልቶችን የሚያስተምሩ ከሆነ፣

ሐ. የምንባቡ ይዘት ከተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ ጋር የሚሄድ ከሆነ ፣

መ. ምንባቡ በክፍል ውስጥ ለሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ለተለያዩ ክንዋኔዎች አመቺ ከሆነ፣ ምንባቡን መመረጥ እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ Wallace እነዚህ መለኪያዎች ሙሉ በሙሉ ተሳክተው ባይገኙም በከፊል የሚያሟሉ ከሆነ መምረጥ እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

ከላይ በተገለፀው መለኪያዎች አማካኝነት ምንባቦቹ ከተለያዩ ምንጮች የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የተመረጡት ምንባቦች በስዕል፣ የተደገፉ፣ የረጅም መልዕክቶችን ፍፃሜ ለማወቅ የሚያጓጉ፣ ለደረጃው የሚመጥኑ፣ የአንዳዶቹ ፍቺ ከዐውዳቸው ሊታወቁ የሚችሉ፣ ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ለማዘጋጀት አመቺ የሆኑ፣ ከተማሪቹ እውቀት አድማስ ጋር የሚጣጣም ይዘት በአጥኝዋ ተዘጋጅተዋል፡፡ ከላይ በተገለፀው መስፈርት መሰረት የቋንቋ ትምህርት መምህራን ተገምግሟል፡፡ ለተጠኚ ቡድኖቹ የተዘጋጁት ምንባቦችና የጥያቄዎቹ መልመጃዎች ኮፒ ተደርጎ በልምምድ ወቅት ለእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪዎች ተበትኗል፡፡

በሙከራው ወቅትም ሁለቱም ቡድኖች የክፍል ደረጃቸውን የሚመጥን ተመሳሳይ የትምህርት ይዘት የሚማሩ ሲሆን በመማር ማስተማሩ ደረጃ የትምህርት ልምዶች አቀራረብ ልዩነት እንዳይፈጠር መርሃ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ መካሄድ እንዳለበት ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን አላማ መሰረት በማድረግ መረጃዎች የተጠናቀሩት በሚከተለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡

1. ፈተና

### 3.4.1. ፈተና

የፈተና አዘገጃጀትና አፈታተን በችሎታ መበላለጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተጠኚ ቡድኖችን ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና በመስጠት ነው፡፡

ያለው (2009፣194) እንደገለፀው ፈተና የተወሰኑ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ወጥነት ባለው መንገድ የተፈታኞችን አዕምሯዊ ወይም ስነባህሪያዊ ሁኔታ አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ መለኪያ ነው፡፡

አንብቦ መረዳትን መፈተን

በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት ሲታሰብ የሚከተሉትን ችሎታዎች የሚጠይቅ ነው ፡፡

- የቋንቋ ምልክቶችን መገንዘብ
- ጽንሰ ሀሳብን መረዳት
- የደራሲውን ድምጸትና የአፃፃፍ ስልት ማወቅ

የአንብቦ መረዳት ፈተና ከላይ የተጠቀሱትን ችሎታዎች የሚፈትን ነው ።ፈተናውም የሚመሰረተው በጥንቃቄ በተመረጡ አጠር አጠር ያሉ በአፃፃፍ ስልት በይዘትና በክብደት በተለያዩ ምንባቦች ላይ ነው ።

### 3.4.1.1. ቅድመ ትምህርት ፈተና

ለተማሪዎች የቅድመ ችሎታ ትምህርት ፈተና በአጥኚዋ ተዘጋጅቶ ተስጥቷል። ፈተናዎቹም በመምህራኖች ተገምግሟል። የተዘጋጁት የተማሪዎቹን እውቀት፣ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌና ክሂልን መሰረት በማድረግ ነው። ፈተናው አምስት ክፍል ያለው ሲሆን፣ የመጀመሪያው ክፍል እውነት ሐሰት በል /ይ / ሁለተኛው ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚመለሱ ጥያቄዎች በሶስተኛው ተመሳሳይ ፍቺ ፃፍ /ፊ/ አራተኛው አረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ መምረጥ አምስተኛው አያያዥ ቃላትን መጠቀም ናቸው። አባሪ <u>ሀ</u> ተመልከቱ

ጥያቄዎቹ በዚህ መልክ ተዘጋጅተው 40 ጥያቄዎችን አካተዋል። ፈተናው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ለማወቅ የታለመ በመሆኑ ተማሪዎቹ ጥያቄዎን ከመመለሳቸው በፊት በመምህራኖች ምንባቡን በጥሞና ማንበብ እንዳለባቸው ተገልፆላቸዋል። በተጨማሪም ፈተናውን በተገቢው መንገድ በጥንቃቄ ተሰብስቦ ከታረመ በኃላ በተገኘው ውጤት መሰረት በሁለቱም ቡድኖች መካከል የችሎታ መበላለጥ የማይታይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ሰንጠረዥ <u>3 እና 4</u> ይመልከቱ።

### 3.4.1.2. የትግበራ ሂደት

ለተጠኚም ቡድኑም ሆኑ ለቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ፈተና ከተሰጠ በኃላ የመምህራኑ ፍቃደኝነት እና ትብብር ተጠይቆ ለምንባቡ ስእል በማሳል የቁጥጥር ቡድኑን ያለ ስዕላዊ የትምህርት መረጃ መሳሪያ ብቻ እንዲማሩ፤ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም እንዲማሩ ለሰባትት ተከታታይ ሳምንታት ሁለቱንም ቡድኖች በሳምንት ሁለት ጊዜ ለ14 ክፍል ጊዜያት ተመሳሳይ ምንባብ ቀርቦላቸው ከህዳር 19 እስከ ጥር 5 ድረስ ልምምዱን እንዲከታተሉ ተደርጓል።

### 3.4.1.3. የድህረ ትምህርት ፈተና

የድህረ ትምህርት ፈተና አላማ በስዕላዊ" የትምህርት መርጃ መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መሻሻሉን ለማየት የሙከራ ቡድኑ የውጤት ብልጫ አሳይተው እንደሆነ እና እንዳልሆነ ለማወቅ ነው። የአንብቦ መረዳት ችሎታው በምንባቡ በግልጽ በስውር የቀረቡ ሀሳቦችን መረዳት ፣የቃላትና የሀረጋትን አውዳዊ ፍቺ፣ የምንባቡን ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት ለማየት ሲሆን ፈተናዎቹም በመምህራኖች ተገምግሟል። ጥያቄዎቹ

በዚህ መልክ ተዘጋጅተው 40 ጥያቄዎችን አካተዋል። ፈተናው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ለማወቅ የታለመ በመሆኑ ተማሪዎቹ ጥያቄዎችን ከመመለሳቸው በፊት በመምህራኖች ምንባቡን በጥሞና ማንበብ እንዳለባቸው ተገልፆላቸዋል። ፈተናውን በጥንቃቄ እንዲሰሩ አስፈላጊ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል። ፈተናው ተባዝቶ ለተማሪዎች ከመሰራጨቱ በፊት አማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን ተገምግሞ በተሰጠው አስተያየት ተሻሽሎ ቀርቧል። ፈተናው ከተዘጋጀ በኃላ የቁጥጥሩም ሆነ የሙከራው ቡድን አባላት በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት 50' ደቂቃ ተሰጥቷቸው እንዲፈተኑ ተደርጓል።

የፈተናዎች አዘገጃጀት እውነት ሐሰት በል/ይ/ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች፣ተመሳሳይ ፍቺ፣ አረፍተነገር ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ መጻፍና አያያዥ ቃላት ናቸው። <u>አባሪ ለ</u> ይመልከቱ ። የቅድመና የድህረ የፈተናዎች መልስ በተዘጋጀው የማረሚያ መስፈርት በሶስት መምህራኖች ታርሟል <u>“አባሪ” መ እና ሠ</u> ይመልከቱ።

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና እና የተሰበሰቡ የጥናት መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው የማብራራት ስራ ከተከናወነ በኃላ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት እና በስዕላዊ መርጃ መሳሪያ ተጠቅሞ ማስተማር እና ያለ ስዕላዊ መርጃ መሳሪያ ማስተማርን በማነፃፀር ደግም ልኬት /Repeated Measures T-test/ ቀመር አማካኝነት በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰርቷል። በጥናት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመንተንተን ና መጠናዊ መረጃ መተንተኛ ዘዴም ስራ ላይ ውሏል ። ጥናቱ መጠነዊ መርጃ መተንተኛ ዘዴዎች ወይም ስልትን የተከተለበት ምክንያትም የጥናቱን ርዕሰ ጉዳዮች ለመግለፅ የሚያስችሉ ዘዴዎች በመሆናቸውና በፈተና የተሰበሰቡትን ለመተንተን ምቹ ተብለው በመታሰባቸው ነው። በፈተና የተገኙ መረጃዎች በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል። ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በቁጥር የሚተነተኑ በመሆናቸው ነው። ያለው (2009፣301) እንደገለፀው ዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ከአንድ ናሙና ላይ በቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና በመስጠት መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ አድርገን ስንጠቀም የናሙና ባህሪ በሁለቱ ልኬቶች ወቅት ወጥ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን ያስችላል ። ከላይ በተገለፀው መሰረት ተሳታፊዎች በስዕላዊ መርጃ መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከመማራቸው በፊትና ከተማሩ በኃላ በአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ለውጥ ማምጣታቸውንና አለማምጣታቸውን ለመፈተሽ ሲባል ቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና በመጠቀም የተገኘው መረጃ በተገቢው ሁኔታ ለመሰበሰብ፣ ለማወዳደርና በስእላዊ መርጃ መሳሪያ የተማሩት አንብበው መረዳት ችሎታ ለማዳበር ሲባል ነው።

# ምዕራፍ አራት

# 4 የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽዎ በሙከራ መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥም በምዕራፍ ሶስት በተገለፀው መንገድ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ የጥናቱን ውጤት የሚያሳዩ መረጃዎችም በፈተና አማካይነት ተሰብስበዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍም ከቅድመ ፈተናው፣ ከድህረ ፈተናው የተገኙት መረጃዎች ተተንትነዋል፤ ትንተናዎቹ ያመላከቱት ውጤትም ተብራርቷል፡፡

## 4.1. የመረጃ ትንተና

### 4.1.1. የቅድመ ፈተና ውጤት ትንተና

በምዕራፍ ሶስት እንደተገለፀው ቅድመ ፈተናው የተማሪዎችን የቅድመ ችሎታ ትምህርት ፈተና በአጥኝዋ ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል፡፡ ፈተናዎቹ የተዘጋጁት የተማሪዎቹን እውቀት፣ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌና ክሂልን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በቅድመ ፈተናው ለመለካት የተፈለገው ጉዳይ ሁለቱ ቡድኖች ተቀራራቢ የቋንቋ ችሎታ ላይ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ነው፡፡ ቅድመ ፈተና ከተሰጠ በኋላ በሶስት አራሚዎች ታርሞ አማካይ ነጥባቸው ተመዝግቧል፡፡ የጥያቄ አይነት ተማሪዎች ያስመዘገቡትን ነጥብ በመተንተን ሁለቱ ቡድኖች ያላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተተንትኗል፡፡ በመሆኑም ከቅድመ ፈተናው የተገኘው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሰንጠረዥ1፦ቅድመ ትምህርት ፈተና የተማሪዎች ቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ

የጉልህነት ደረጃ (significant level) *P>0.05

| | ቡድኖቹ (group) | ናሙና (N) | አማካይ (Mean) | መደበኛ ልይይት (Std. D) | መደበኛ የስህተት አማካይ Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | 48 | 59.4792 | 6.78230 | .97894 |
| | የሙከራ ቡድን | 48 | 59.3542 | 5.65117 | .81568 |

ሰንጠረዥ አንድ የሰፈረው የቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ እንደሚያመለክተው የተማሪዎች መረዳት ችሎታ ጥያቄዎች በእውነት ወይም ሐሰት የአንብቦ መረዳት ግልፅና ስውር ሀሳቦችን፣ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት ጥያቄዎችን መመለስ፣ አዛምድ፣ አያያዥ ቃላትን ባዶ ቦታ ሙሉ እንዲሁም የቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ጥያቄዎች ምርጫ የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ተቀራራቢ አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህም ሲባል የቁጥጥር ቡድኑ 59.47 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ 59.35 የሚሆን አማካኝ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይሁን እንጂ የቡድኖቹን አማካይ ውጤት በመመልከት ብቻ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት እውቀት ችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በመሆኑም ይህንን ለማረጋገጥ ሁለቱ ቡድኖች በእያንዳንዱ የአንብቦ መረዳት የመመዘኛ ጥያቄ አይነት ያመጡትን ውጤት በባእድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት መተንተን አስፈላጊ በመሆኑ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ተተንትኗል፡፡

**ሰንጠረዥ 2 ፦ ቅድመ ትምህርት ፈተና የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት የባእድ ናሙናዎች ቲ- ቴስት**

| | | የሌቨኔ የልይይቶች እኩልነት መሞከሪያ | | የአማካይ እኩልነት ቲ-ቴስት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የልይይት ዋጋ (f) | ጉልህነት (sig.) | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (D/f) | ጉልህነት (ባለ ሁለት ጫፍ) | የአማካይ ልዩነት | መደበኛ የስህተት ልዩነት | 95% የምናልባት ስህተት መተማመኛ | |
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | እኩል ልይይት ይኖራል | .787 | .377 | .098 | 94 | .922 | .12500 | 1.27423 | -2.40501 | 2.65501 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | .098 | 91.036 | .922 | .12500 | 1.27423 | -2.40608 | 2.65608 |

ቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ 2.00

በሠንጠረዥ ሁለት የተገለፀው በዳግም ልኬት ናሙና (Repeted meaur sample t-test) ከአንድ ናኑና ላይ ቅድመ ፈተናን (pre test 1) እና ድህረ ፈተናን (post test 1) የመረጃ ዘዴ አድርገን ስንጠቀም የናሙናው ባህሪ በሁለት ልኬቶች ወቅት ወጥ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን ያስችለናል፡፡ (ያለው 2009፣301) በቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤትም ሆነ ድህረ ትምህርት ፈተና የእያንዳንዱ የጥያቄ አይነት ውጤት በአጥኚዋ የተሰራ ነው፡፡ የባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስትን ለመተንተን እነዚህን መረጃዎች መሰረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በተሰጠው የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) በዚህም የቲ ዋጋ 0.98 በመሆኑ ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋ ያንሳል፡፡ በመሆኑም የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የ‹p› (ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት) ዋጋ ከ0.05 (መደበኛ የጉልህነት ደረጃ) የሚያንስ ከሆነ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የ‹p› ዋጋ ከ0.05 የሚበልጥ ከሆነ በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክተል፡፡ በመሆኑም የ‹p› (ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት) ዋጋ 0.922 በመሆኑ ከ0.05 (መደበኛ የጉልህነት ደረጃ) ስለሚበልጥ ጉልህ ልዩነት የላቸውም፡፡

በእዚህ እሳቤ መሰረት በሰንጠረዥ ሁለት የሰፈረው የባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት እንደሚያመለክተው በአምስቱ የፈተና አይነቶችም ሆነ በሁሉም የጥያቄ አይነቶች ድምር ውጤት ትንተና በ94 የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) የቲ ዋጋ ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ያንሳል፡፡ እንዲሁም የባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት ዋጋ ከ0.05 ይበልጣል፡፡ ይህም በሁለቱ

ቡድኖች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት እውቀት ልዩነት እንደሌለ ያመለክታል። በመቀጠል ደግሞ የተማሪዎችን ለሰባት ሳምንት ለአስራ አራት ክፍለ ጊዜ ልምምድ ካደረጉ በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡደኖች ተሰጥቷል። ድኅረ ትምህርት ፈተናው እንደ ቅድመ ትምህርት ፈተናው ተመሳሳይነት ያለው ነው። በመቀጠል ድህረ ትምህርት ፈተና ጥያቄዎች የሁለቱ ቡድኖች ውጤት ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 4.1.2. የድህረ ፈተና ውጤት ትንተና

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የሙከራ ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት እውቀት ችሎታቸውን ተመሳሳይ ችሎታ እንዳላቸው በቅድመ ፈተና ውጤት ትንተና ተረጋግጧል። የተመረጠውን ምንባብ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት እውቀት ትምህርቱን በተቀናጀ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ዘዴ ሲማሩ የቁጥጥር ቡድኑም ተማሪዎች ደግሞ ያንኑ ምንባብ ያለስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በተለመደው የአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ መንገድ ተምረዋል።

ትምህርቱ ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለአንብቦ መረዳት፣ ከትርጉሙና ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለአንብቦ መረዳት ክሒል ማሳደግ አለማሳደጉን ለመገምገም የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ያካተተ ድህረ ፈተና በማዘጋጀት የሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ተፈትነዋል። ፈተናው የታረመው እንደ ቅድመ ትምህርት ፈተና ሁሉ በሶስት መምህራን የታረመ ሆኖ አማካያቸው ተወስዷል። ያመጡት ውጤት ለየብቻቸው ተተንትነዋል።

#### 4.1.2.1. የአንብቦ መረዳት እውቀት መመዘኛ የድህረ ፈተና ጥያቄዎች ውጤት ትንተና

በጥናቱ ዘዴ እንደተገለፀው የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት እውቀት የሚመዝኑ አምስት የጥያቄ አይነቶች በድህረ ፈተናው ሲኖሩ ከስልሳ በሶስት አራሚ ታርሞ አማካኙ ተወስዷል። ቀጥሎ የሙከራ ቡድን ተማሪዎችና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በእያንዳንዳቸው የጥያቄ አይነቶች እና በድምር የአንብቦ መረዳት እውቀት መመዘኛ ጥያቄዎች ያመጡት ውጤት በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክ እና በባእድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት በተከታታይ ተተንትነዋል።

## ሰንጠረዥ 3፡- ድህረ ትምህርት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝርዝር ንዑሳን ክሂል ጥያቄዎች ቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ

Group Statistics

| የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች | ቡድኖቹ (group) | ናሙና (N) | አማካይ (Mean) | መደበኛ ልይይት (Std. D) | መደበኛ የስህተት አማካይ Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| በምንባቡ በግልፅ እና በሥውር የቀረቡ ሃሳቦችን መረዳት | የሙከራ ቡድን | 48 | 23.4583 | 3.09398 | .44658 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 48 | 18.6458 | 3.92206 | .56610 |
| የቃላትንና የሀረጋትን አውዳዊ ፍቺ መረዳት | የሙከራ ቡድን | 48 | 25.4583 | 2.24042 | .32338 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 48 | 18.0833 | 4.36540 | .63009 |
| የምንባቡን ዋናና ዝርዝረ ሃሳቦች መረዳት | የሙከራ ቡድን | 48 | 16.3333 | 1.71766 | .24792 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 48 | 14.7083 | 2.75185 | .39720 |
| አያያዥ ቃላትና ሐረጋትን መረዳት፣ | የሙከራ ቡድን | 48 | 16.9583 | 1.79785 | .25950 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 48 | 15.1250 | 2.702444 | .39006 |

በሰንጠረዥ ሶስት የሰፈሩት ስታስቲካዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በአምስቱም የፈተና አይነቶች መመዘኛ ጥያቄዎች በምንባቡ በግልፅ እና በሥውር የቀረቡ ሃሳቦችን መረዳት፣ የቃላትንና የሀረጋትን ተመሳሳይና አውዳዊ ፍቺ መረዳት፣ የምንባቡን ዋናና ዝርዝረ ሃሳቦች መረዳት፣ አያያዥ ቃላትና ሐረጋትን መረዳት፣ በእያንዳንዱ ንዑሳን ክሂል ድምር ውጤት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህ ውጤት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ ውጤት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት እውቀት ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ቡድኖቹ በእያንዳንዱ የጥያቄ አይነትና በድምር የአንብቦ መረዳት መመዘኛ ጥያቄዎች ያመጡት ውጤት በባእድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ቀጥሎ ተተንትኗል፡፡

**ሰንጠረዥ 4 ፡-ድህረ ትምህርት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝርዝር ንዑሳን ክሂል ጥያቄዎች ውጤት የባእድ ናሙናዎች ቲ- ቴስት**

Independent Samples Test

| የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች | | የሌቨኔ የልይይቶች እኩልነት መሞከሪያ | | የአማካይ እኩልነት ቲ-ቴስት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የልይይት ዋጋ (f) | ጉልህነት (sig.) | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (D/f) | ጉልህነት (ባለ ሁለት ጫፍ) | የአማካይ ልዩነት | መደበኛ የስህተት ልዩነት | 95% የምናልባት ስህተት መተማመኛ | |
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| በምንባቡ በግልፅ እና በሥውር የቀረቡ ሃሳቦችን መረዳት | እኩል ልይይት ይኖራል | 11.600 | .001 | -3.471 | 94 | .001 | -.81250 | .23411 | -1.27733 | -.34767 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -3.471 | 78.796 | .001 | -.81250 | .23411 | -1.27850 | -.34650 |
| የቃላትንና የሀረጋትንና አውዳዊ ፍቺ መረዳት | እኩል ልይይት ይኖራል | 5.978 | .016 | -3.825 | 94 | .000 | -.89583 | .23419 | -1.36082 | -.43085 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -3.825 | 81.750 | .000 | -.89583 | .23419 | -1.36173 | -.42994 |
| የምንባቡን ዋናና ዝርዝረ ሃሳቦች መረዳት | እኩል ልይይት ይኖራል | .677 | .413 | -6.508 | 94 | .000 | -3.14583 | .48339 | -4.10561 | -2.18606 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -6.508 | 89.383 | .000 | -3.14583 | .48339 | -4.10626 | -2.18541 |
| አያያዥ ቃላትና ሐረጋትን መረዳት | እኩል ልይይት ይኖራል | 16.852 | .000 | -10.390 | 94 | .000 | -4.91667 | .47320 | -5.85622 | -3.97711 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -10.390 | 71.747 | .000 | -4.91667 | .47320 | -5.86004 | -3.97330 |

የአንብቦ መረዳት ዕውቀት ለመመዘን ከቀረቡት የጥያቄ አይነቶች ውስጥ ከምርጫ ጥያቄዎች ውጭ ባሉት የፈተና አይነቶችና በድምር የአንብቦ መረዳት ዕውቀት መመዘኛ ጥያቄዎች በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የችሎታ ልዩነት እንዳለ በሰንጠረዥ አራት የቀረቡት ቁጥራዊ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በምንባቡ በግልፅ እና በሥውር የቀረቡ ሃሳቦችን መረዳት፣ ሰላሳ ነጥብ የያዙ ጥያቄዎች በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል የ0.8125 የአማካይ ውጤት ልዩነት አለ፡፡ ይህም ማለት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት በ 0.8125 ይበልጣል ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቲ ዋጋ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.000 በልጦ 3.475 ሆኗል፡፡ እንዲሁም ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት ከ0.05 አንሶ 0.001 ሆኗል፡፡

በመቀጠል አምስት ጥያቄዎች የቃላትንና የሀረጋትን አውዳዊ ፍቺ መረዳት፣ በቀረቡት አምስት የአዘምድ ጥያቄዎች በሙከራ ቡድን ተማሪዎች እና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የችሎታ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት አዛምድ ጥያቄዎች የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ አማካይ ውጤት እንደሌላቸው ነው፡፡ በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል የጥያቄ አይነቱን በመስራት ጉልህ የሆነ የችሎታ ልዩነት የለም ማለት ነው፡፡

ከምርጫ ጥያቄ በመቀጠል በድህረ ፈተናው የሰፈረው የአንብቦ መረዳት ዕውቀት የመመዘኛ የጥያቄ አይነት ሃያ ነጥቦችን የያዘው *የምንባቡን ዋናና ዝርዝረ ሃሳቦች መረዳት፣* የሚለው ነው፡፡ በዚህ የጥያቄ አይነት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት በ3.14583 ይበልጣል፡፡ እንዲሁም የቲ ዋጋ ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ሲበልጥ፣ ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነቱ ደግሞ ከ0.05 (መደበኛ የጉልህነት ደረጃ) ያንሳል (ቲ= 6.508 ፤ የ‹p› ዋጋ= 0.000)፡፡ በዚህ የትንተና ውጤት መሰረትም ዋና ንዑስ ሃሳቦችን መለየት በሚለውን የጥያቄ አይነት በመስራት በሙከራ ቡድን ተማሪዎች እና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የችሎታ ልዩነት አለ፤ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ የጥያቄ አይነቱን የመስራት አቅም አላቸው፡፡

ሶስተኛ የአንብቦ መረዳት ዕውቀት መመዘኛ የድህረ ፈተና የጥያቄ አይነት አስር ነጥብ የያዘ ሲሆን *የአያያዥ ቃላትና ሐረጋትን መረዳት፣*መለየት የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ የጥያቄ አይነት በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት መካከል የ4.91667 ልዩነት አለ፡፡ ከአማካይ ውጤት በተጨማሪ የቲ ዋጋ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.000 በልጦ 10.390 ሲሆን ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነቱ ደግሞ ከ0.05 አንሶ 0.000 ሆኗል፡፡ ይህም የሚያሳየው የተለያዩ *የአያያዥ ቃላትና ሐረጋትን መረዳት* የጥያቄ አይነት በሙከራ ቡድን ተማሪዎችና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የችሎታ ልዩነት መኖሩንና የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ *የአያያዥ ቃላትና ሐረጋትን መረዳት፣* አቅም እንዳላቸው ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 5፡- ድህረ ትምህርት የተማሪዎች ጥቅል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጥያቄዎች**

**ቡድናዊ ገላጭ ስታስቲክስ**

| | ቡድኖቹ (group) | ናሙና (N) | አማካይ (Mean) | መደበኛ ልይይት (Std. D) | መደበኛ የስህተት አማካይ Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| ድህረ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ቡድን | 48 | 82.3958 | 7.06426 | 1.01964 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 48 | 66.4533 | 12.18642 | 1.75896 |

በሰንጠረዥ አምስት የሰፈሩት ስታስቲካዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአምስቱ የፈተና አይነቶችም ሆነ በአጠቃላዩ በአንብቦ መረዳት መመዘኛ ጥያቄዎች ድምር ውጤት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህ ውጤት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ ውጤት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በቅድመ ፈተና ውጤት ትንተና ክፍል እንደተገለፀው የቡድኖቹን አማካይ ውጤት በመመልከት ብቻ በቡድኖቹ መካከል ጉልህ የችሎታ ልዩነት አለ ወይም የለም ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት እውቀት ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ቡድኖቹ በእያንዳንዱ የጥያቄ አይነትና በድምር የአንብቦ መረዳት መመዘኛ ጥያቄዎች ያመጡት ውጤት በባእድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ቀጥሎ ተተንትኗል፡፡

**ሰጠረዥ 6 ፡-ድህረ ትምህርት የተማሪዎች ጥቅል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጥያቄዎች ውጤት የባእድ ናሙናዎች ቲ- ቴስት**

| | | የሌቨኔ የልይይቶች እኩልነት መሞከሪያ | | የአማካይ እኩልነት ቲ-ቴስት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የልይይት ዋጋ (f) | ጉልህነት (sig.) | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (D/f) | ጉልህነት (ባለ ሁለት ጫፍ) | የአማካይ ልዩነት | መደበኛ የስህተት ልዩነት | 95% የምናልባት ስህተት መተማመኛ | |
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ድህረ ትምህርት ፈተና | እኩል ልይይት ይኖራል | 8.813 | .004 | -7.933 | 94 | .000 | -9.79167 | 1.23426 | -12.24232 | -7.34101 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -7.933 | 76.828 | .000 | -9.79167 | 1.23426 | -12.24948 | -7.33385 |

የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ፡ 2.000

በሠንጠረዥ ስድስት መረዳት እንደሚቻለው የሌቨኔ የልይይቶች እኩልነት መሞከሪያ ላይ የተገለፀው የጉልህነት ደረጃ (significant level) በሁሉም የጥያቄ አይነቶችና የአንብቦ መረዳት ችሎታ እውቀት መመዘኛ ድምር ውጤት ከ0.05 ያንሳል፡፡ የባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስትን ለመተንተን እነዚህን መረጃዎች መሰረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በተሰጠው የነፃነት ደረጃ (degree of freedom) የቲ ዋጋ(-7.933) ሲሆን ኔጌቲቭ ቢሆንም የማንኛውም ቁጥር ፈፁም ዋጋ ፖዘቲቭ በመሆኑ ፍፁም ዋጋውን በመውሰድ ቲ(7.933) ሆኗል፡፡ ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከበለጠ ወይም እኩል ከሆነ፣ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የ‹p› (ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት) ዋጋ ከ0.05 (መደበኛ የጉልህነት ደረጃ) የሚያንስ ከሆነ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የ‹p› ዋጋ ከ0.05 የሚበልጥ ከሆነ በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክተል፡፡ በመሆኑም የ‹p› (ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት) ዋጋ .000 በመሆኑ ከ0.05 (መደበኛ የጉልህነት ደረጃ) ስለሚያንስ የጎላ ልዩነት አላቸው፡፡

በእዚህ እሳቤ መሰረት በሰንጠረዥ ስድስት የሰፈረው የባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት እንደሚያመለክተው ስዕላዊ ትምህርት መርጃ ለአንብቦ መረዳት ክሂል ያለውን አስተዋጾ

በተደረገው ሙከራ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት እውቀት ልዩነት እንዳለ ያመለክታል፡፡

ከላይ የተብራሩት የአንብቦ መረዳት ዕውቀት ለመመዘን የተዘጋጁ አምስት የፈተና አይነቶች የያዟቸው ውጤቶች ሲደመሩ መቶ ነጥብ አላቸው፡፡ ይህ ጥናት በአንብቦ መረዳት እውቀት ያካለለውን ወሰን ያካተቱ ጥያቄዎችን ድምር ውጤት ያሳያል፡፡ ከላይ በእያንዳንዱ የፈተና አይነት የተብራሩትን ነጠላ ውጤቶች በአንድ ላይ በመደመር የተገኘው አጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ዕውቀት መመዘኛ የድህረ ፈተና ድምር ውጤት ማብራሪያ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

በሰንጠረዥ ስድስት የሰፈረው የባእድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት እንደሚያመለክተው ስልሳ ነጠብ በያዘው አጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ዕውቀት መመዘኛ ጥያቄዎች ውጤት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት በ9.79167 ይበልጣል፡፡ እንዲሁም የቲ ዋጋ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.000 በልጦ 7.933 ሲሆን ባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነቱ ከ0.05 አንሶ 0.000 ሆኗል፡፡ በሙከራ ቡድን ተማሪዎችና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት ዕውቀት ልዩነት እንዳለ እነዚህ ስታቲስቲካዊ መግለጫዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም በመነሳት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከሙከራ ትምህርቱ በኋላ የአንብቦ መረዳት እውቀታቸው አድጓል ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ዕውቀት ለመመዘን ከተዘጋጁት አምስት የጥያቄ አይነቶች ድምር ውጤት የተደረጉት ትንተናዎች እንደሚያመለክቱት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ የአንብቦ መረዳት ዕውቀት አላቸው፡፡ ይህንንም የአንብቦ መረዳት ዕውቀት ልዩነት ያመጣው በስዕላዊ ትምህርት መረጃ መሳሪያ መጠቀም ከአገልግሎቱ ጋር በማቀናጀት ማስተማር ነው፡፡

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካት መረጃዎች በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተሰበሰቡ ሲሆን ከጥናቱ ባህሪ ጋር በሚሔዱ የመተንተኛ ስልቶችም ተተንትኗል፡፡ በመረጃዎቹ ትንታኔ መሰረት የጥናቱ ውጤት ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሀዋሪያው ጰጥሮስ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ማስተማር የአንበቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ነው፡፡ በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና በተገኘው አማካይ ውጤት መሰረት ሁለቱ ቡድኖች ከልምምዱ በፊት የጎላ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው የስታስቲክ ስሌቱ ($p>0.05$) አረጋግጧል፡፡

በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት እውቀት ክሒል ልዩነት እንደሌለ ከተረጋገጠ በኂላ የሙከራ ትምህርቱ ለሰባት ሳምንታት (ለአስራ አራት ክፍለ ጊዜዎች) ተሰጥቷል፡፡ ከሙከራ ትምህርቱ በኂላ የጥናቱን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ያካተተ ድህረ ፈተና ተሰጥቶ ውጤቱን በመውሰድ የድህረ ፈተና ውጤት ትንተና ተካሂዷል፡፡ የውጤት ትንተናው እንዳመለከተውም በሙከራ ቡድን ተማሪዎችና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት እውቀት ክሒል የአቅም ልዩነት አለ ($p < 0.05$) ፡፡

ይህም ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ስልትን መተግበር አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማዳበር አስተዋፅኦ አለው ወደ ሚለው መደምደሚያ ሊደርስ ይችላል፡፡ ለውጡ የመጣው አንብቦ የመረዳት ክሂልን ሲማሩ የቀረበላቸውን መሣሪያ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ አቀራረብ ስልትን በመተግበር ካዳበሩት ሀሳብ የመጣ ይመስላል፡፡ ይህም ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ስልት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ማጎልበቻ እንደሆነ ለጥናቱ ውጤት የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሙከራ ቡድኑ በአስራ አራት የትምህረት ክፍል ተደራጅቶና ተቀናጅቶ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ስልት በተዘጋጀ መሣሪያ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ተምረዋል፡፡ በአንፃሩ የማመሳከሪያ ቡድኑ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው ጽሁፍ የአንብቦ የመረዳት ክሂልን እንዲማሩ ተደርጓል፤ በኂላም የሁለቱ ቡድኖች የችሎታ ልዩነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመለየት በድህረ ትምህረት ፈተናው እያንዳንዱ ተማሪ በንዑሳን ክሂሎቹ ያመጣው ተናጠላዊ ውጤት በባዕድ ናሙና (ቲ-ቴስት) (independent samples t-test) ተፈትሿል፡፡ከትንተናው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ  በጥቅል ውጤት

የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከመቶ 82.3958 ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ በአንጻሩ 66.4583 ነው፡፡ ይህ ደግሞ የጎላ ልዩነት እንዳላቸው ያስረዳል፡፡ (p<0.05) በምንባቡ በግልፅ እና በሥውር የቀረቡ ሃሳቦችን መረዳት በሚለውን ዑሳን ክሂል (8.1667) ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (7.3542) ጋር ሲነፃፀር የጎላ ልዩነት እንዳላቸው የስታስቲክ ስሌቱ (p<0.05) የቲ ዋጋ(-7.933) ሲሆን ኔጌቲቭ ቢሆንም የማንኛውም ቁጥር ፈፁም ዋጋ ፖዘቲቭ በመሆኑ ፍፁም ዋጋውን በመውሰድ ቲ(7.933) ሆኗል፡፡ ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከበለጠ ወይም እኩል ከሆነ፣ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ በዚህም ልዩነት መኖሩ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በመቀጠልም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት፣ የቃላትና የሐረጋትን ተመሳሳይ ፍቺና አውዳዊ ፍቺ መረዳት እና የአያያዥ ቃላትና ሐረጋትን አገልግሎት መገንዘብ በሚሉት አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎች በስታስትክ ስሌቱ የጎላ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህንንም ልዩነት የፈጠረው አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂልን በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ስልት የተለያዩ ተግባራትን በመማራቸው ነው ቢባል ምክንያታዊ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ስልት የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂል ለማሳደግ አስተዋፆኦ አለው ለማለት ይቻላል፡፡ ውጤቱም ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ስልትን በመተግበር ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂልን በማሻሻል ረገድ ያለውን ጠቀሜታ ካቀረቡት ንድፈ ሀሳብ ጋር የጥናቱ ውጤት የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡ ለጥናቱ ጥያቄዎች አወንታዊ ምላሽ አስገኝቷል ማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. የጥናቱ ማጠቃለያ፣መደምደሚያ እና አስተያየት

## 5.1. የጥናቱ ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሀዋሪያው ጴጥሮስ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ማስተማር የአንበቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ስለመሆኑ በቀዳሚዎቹ ምዕራፎች ተገልጿል፡፡ ለዚህም ጥናቱ በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልትን ከተለምዷዊው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ስልት ሲነፃፀር በተማሪዎች ውጤት ላይ የሚያሳየውን ለውጥ በሙከራ ለማረጋገጥ ያለመ ሲሆን ለሚከተሉት የጥናቱ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

1. በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልትን በመተግበር አንብቦ የመረዳት ክሂልን በተማሩትና በተለምዷዊ ማንበብን የማስተማሪያ ዘዴ በተማሩ ተማሪዎች መካከል የውጤት ልዩነት ይኖር ይሆን?
2. ስልቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል በማሻሻል ረገድ በንኡስ ክሂል ውጤት ያሳድግ ይሆን?
3. ተማሪዎች በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ከተማሩ በኋላ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን ለማዳበር ይችሉ ይሆን?

ለጥናቱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠትና መላምቶችንም ለመፈተሽ የጥናቱ ተሳታፊዎች ተመርጠው በታቀደላቸው መሰረት ተምረዋል፡፡ልዩ ልዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተዘጋጅተው መረጃዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርትፈተና እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡

በዚሁ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ፣ወረዳ 06 በሚገኘው የሀዋሪያው ጴጥሮስ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓመተ ምህረት በአራተኛ ክፍል ሁለት ክፍሎችን በመምረጥ 96 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡ በሁለቱ ቡድን የተመደቡት በተራ እጣ ናሙና ዘዴ ከተለዩ በኋላ 48 ተማሪዎች በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልትን በመተግበር በሙከራ ቡድኑና ቀሪዎቹ 48 ተማሪዎች ደግሞ በተለምዷዊው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ስልት

በማመሳከሪያ ቡድን በእጣ ተመድበዋል፡፡ ስብጥራቸውን በተመለከተ በናሙና ብዛት፣ በጾታ፣ ተመጣጣኝ ጥንዶች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ከዚያም ሁለቱም ቡድኖች በተመደቡላቸው የአንብቦ መረዳት መማሪያ ተግባራት በትምህርት ቤቱ በማስተማር ላይ በሚገኙት የአማርኛ ቋንቋ መምህርት በ7 ሳምንታት ውስጥ ለ14 ክፍለ ጊዜያት ከአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሒል (በምንባቡን በግልፅና በሥውር የቀረቡ ሃሳቦችን መረዳት፣የቃላትና ሐረጋትን በተመሳሳይ ፍቺና አውዳዊ ፍች መረዳት እና የአያያዥ ቃላትና ሐረጋትን አገልግሎት መረዳት) ተመርጠው አንብቦ መረዳትን ተምረዋል፡፡

በሂደቱም የጥናቱ መረጃዎች በልዩ ልዩ መሣሪያዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከመሣሪያዎቹ የማስተማሪያ ማንዋሎቹ በይዘታቸው ለተማሪዎቹ የሚመጥኑ ስለመሆናቸው በደረጃው በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ቅድመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች አቻነት ያላቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን አካተው በአጥኚዋ የተዘጋጁ ነበሩ፡፡ ፈተናዎቹ በባለሙያዎች ግምገማ የተደረገባቸው ሲሆን፣ አስተማማኝነታቸውም በመለካት .0792 ሲሆን፣ድህረ ትምህረት ፈተናው ደግሞ .0991 አስተማማኝነት አሳይቷል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት መረጃዎች ከጥናቱ ተሳታፊዎች ከተሰበሰቡ በኋላም በጥናቱ እንደተነሱት ጥያቄዎች እየታዩ በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክሶች ተተንትነዋል፤

መረጃዎቹ ከተተነተኑ በኋላም በጥናቱ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ የመጀመሪያው የጥናቱ ዓላማ በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልትን በመተግበር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ማዳበር የሚቻል መሆን ወይም አለመሆኑን መመርመር ነው፡፡በውጤቱም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከማመሳከሪያ ቡድን ተማሪዎች የተሻለ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማዳበራቸው ተረጋግጧል፡፡ ገላጭ ድምዳሜያዊ ስታትስቲክ እንዳመላከተው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ስታቲስቲካዊ የውጤት ልዩነት (statistically significant difference) አለ፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ንኡስ ዓላማ ስልቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል በማሻሻል ረገድ ለንኡስ ክሂል አስተዋጽ ያለው መሆኑን መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም ስልቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ውጤታቸውን ማሻሻሉን ለማወቅ የየራሳቸው ዓላማዎች የነበሯቸው አምስት የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ተናጠላዊ ውጤቶች ለየብቻቸው ተተንትነዋል (ሰንጠረዥ «6» ይመልከቱ)፡፡ በምንባቡ በግልፅ እና በሥውር

የቀረቡ ሃሳቦችን መረዳት፣የቃላትና የሐረጋትን ተመሳሳይ ፍቺና አውዳዊ ፍቺ በመረዳት፣ የምንባቡን ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት እና አያያዥ ቃላትና ሐረጋትን አገልግሎት መረዳት ላይ ለውጥ የታየ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 5.2. የጥናቱ መደምደሚያ

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ችግሮቹን ለማቃለል ከሚያስችሉ የማንበብ ትምህርት አቀራረቦች ውስጥ አንዱ በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም ስልትን በመተግበር አንብቦ መረዳትን ማስተማር ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ መጠቀም ስልት ማንበብን መማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና ንዑሳን ክሂሎችን በማሻሻል በኩል ለውጥ ማምጣት ችሏል፡፡በመሆኑም የጥናቱን ውጤት ትንተናና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ስልትን በመተግበር ማንበብን መማራቸው ተማሪዎች በመረጃ ልውውጥ ሂደት፣ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ዕውቀት በሚያገኙት ተግባራዊ ግንዛቤ የአንብቦ መረዳት ውጤታቸውን በጉልህ ደረጃ ያሻሽላል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ተማሪዎች ማንበብን በሚማሩበት ስልት በመተግበር ሂደት በሚያገኟቸው የድጋፍ ተመክሮዎችና እርስ በራሳቸው በሚያደርጓቸው የመረጃ ልውውጥ እንዲተጋገዙና እንዲረዳዱ፣በማህበራዊ ህይወታቸው ችግር ለመፍታት በሚያደረገው ክንውን ስልቱ በንኡስ ክሂል ውጤት ላይ ከፍተኛ ነው፡፡

## 5.3. አስተያየት

ጥናቱ ያነሳቻውን ውጤቶች መሰረት በማድረግ አጥኚዋ የሚከተሉት የመፍትሔ አስተያየቶች አቅርባለች፡፡

ሀ. ለመምህራን፡- በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማያ ስልትን በመተግበር አንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር የሚኖረው አስተዋፅኦ የጎላ እንደሆነ ይህ ጥናት አሳይቷል፡፡ ስለሆነም ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያን የመጠቀም ስልት ትኩረት ተሰጥቶት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ልምምዱን እንዲያደርጉ መምህራን አዘውትረው ቢያበረታቱ ፋይዳው የጎላ ይሆናል፡፡

ለ. ለመማሪያ መጽሐፍት አዘጋጆች፡-የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ በወጉ ይዳብር ዘንድ በአንድ የክፍል ደረጃ የሚደረገው ትግበራ በቂ አይደለም፡፡ተማሪዎች በሌሎች የክፍል ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ክሂልን በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልትን በመተግበር አንብቦ የመረዳት ክሂልን የዘርፉ ባለሙያዎች ትኩረት ሰጥተው መፍተሔ ቢሰጡ መልካም ነው፡፡

ሐ. ለመርሐ ትምህርት አዘጋጆች፡- በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልትን በመተግበር አንብቦ የመረዳት ክሂልን ተማሪዎች ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣እርስ በርስ መረጃ እንዲለዋወጡ በማድረግ፣ ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በሙከራ ትምህረቱ የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ክሂሉን በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልት ቢቀርብ፣የተሸለ ነው ፡፡

መ. ለጥናት አድራጊዎች፡- በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የማስተማሪያ ስልትን በመተግበር የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለውን አስተወፅኦ በጥናቱ ቢረጋገጥም፤ ተመራማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ በተለይ አራቱን የቋንቋ ክሒሎች አቀናጅቶ ከማስተማር አኳያ በስፋት ቢያጠኑ ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህረት አዘጋጆች ብሎም ለቋንቋው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ አጥኝዋ ታምናለች፡፡

# ዋቢ መጽሐፍ

ተስፋዬ ሸዋዬ፡ (1981) ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፡፡

ትክክል ገና (2014) የገበሬው በጎች ወደዬት ተሰወሩ አስደናቂ ታሪክና ሌሎም አስደሳች ተረቶች፡፡

ትምህርት ሚኒስተር፡ (2007) አማርኛ ሰባተኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ አዲስ አበባ (USAID)

ትምህርት ሚኒስተር (2007) አማርኛ ስምንተኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ አዲስ አበባ፡፡ (USAID)

አሰፉ ደሳለኝ (2001) በጎንደር ከተማ አራት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

አዲስ ልሳን ጋዜጣ (2015) የፕላስቲክ ተፅዕኖ፡፡ ጥቅምት 17 ቀን 2015 ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተሸሽሎ የተወሰደ

አጋዤ (2009) የንባብ መፅሀፍ ከ(USAID) (Save the Children) በትምህርት ሚኒስተር እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ የታተመ፡፡

ክብሮም አሰፋ (2005) የራያ ሕዝብ ባህልና ታሪክ አዲስ አበባ ፋርኢት ማተሚያ ቤት፡፡

የኔሰው ደሴ (1990) በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ማዳበር በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋፅኦ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ፤ (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቅ (2009) የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች አተገባበር አዲስ አበባ ተፈራ ስዩም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደረጀ ገብሬ (2013) መራሔ ንባብ የማንበብ ክሂል ማበልፀጊያ አዲስ አበባ፣ አፍሪካ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌታቸው ለገሰ (1992) አዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋ ትምህርት ጥራት በማሻሻል ሊያበረክቱት የሚችለው አስተዋፅኦ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

ጌታቸው ኮቺ (2000) በቦንጋ ከተማ አምስት አንደኛ ትምህርት እርከን ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀምና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ:: (ያልታተመ)

ግርማ ገብሬ (      )የክሂል ማስተማሪያ ሞጁል ያልታተመ::

ዘኒት አህመድ (2003) በደብርሀን ከተማ ሁለት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም አዲ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ያልታተመ

Amare Asgedom, (1998). Teacher's perceptions of educational problem in Ethiopia. In quality education problems in Ethiopian. In quality education in Ethiopian vision for the 21 first century. Proceeding of national conference held in awassa college of teacher education, (July 12-18,1998)

Aggawal J. (1996) Principles Methods and Techniques of teaching Ne-Delhi Vikas Publishing House.

Adjidh.P (2006) Schema Theory Based consideration on pre-reading activities in ESp Text book.

The Asian EFI Journal Teaching Articles Vol 16.

Bestate Terefe (2000) Application of instructional Materials in the primary school of the SNNPR.Unpublished Master's thesis Addis Abba University, Faculty of Education Addis Ababa.

Bowen, B.M. (1982) Look here visual Aids in language teaching Hong Kong Macmillan publishers Ltd.

Davis, A. (2011) Building Comprehension strategies for the primary years.Elean or Curtain Publishing Level cuite 3.

Ephram, hi (2009). Reading comprehension instruction for expositor text in elementary Education Liberty University

Harmer, J.(2001) the practice o English lunaguge teaching londor pearson educational limited

Harison, R.-H and gowin, L.E. (1995) the elementary teacher in action senfransisco. Wad Sworth publishing company Inc.

Henich R. (1996). Instructional Media and Technologies for learning (5$^{th}$ed). New Jersey Prentic-Hall.

Johnson, A. P. (2008). Teaching Reading and Writing A guide Book for Tutoring and Remediating Students New York.

Kochare,S.k (1995) Methods And Techniques Of Teaching New Delhi Streling Publishers.

Malawi institute of education. (2003) continuous assessment. A training manual for educators in Malawi, Domas Malawi institute of education.

Nunan,D (1991) language teaching methodology. a text book for teachers. New york prints – Hall international.

Nkuuhe,J.(1995) instructional media. In Barbara, M.et al. (Eds). Teach your best. A hand book for university lecturers. Nairob intergrated system ltd.pp.66-79

Nuttal C. (1982) Teaching Reading Skills in a Foreign Language Heineman Educational Books.

Ontario Ministry of Education (2003).A guide to effective instruction in Reading Queens Printer for Ontario.

Quist. D. (2000) Primary teaching methods oxford Macmillan publishers limited.

*Tankersley K. (2005) Literacy* strategies for Grade 4-12 Reinforcing the Trades of Reading Association for supervision and curriculum development Alexandria Virginia USA.

Ur P. (1996). A. course in language teaching practices and theory Cambridge Cambridge university press.

Wallace. C. (1992) Reading Language Teaching a scheme for teacher education oxford. University press.

Wright A. (1989). Pictures for language learning. London Longman

# አባሪዎች

**አባሪ ሀ**

**የቅድመ ትምህርት ፈተና**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ**

**የሂዩማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ጋዜጠኝነት እና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**አማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

**ኮድ**

**ለ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ቅድመ ትምህርት ፈተና (100%)**

**የፈተናው መነሻ ሰዓት 3ሰዓት**

**ለፈተና የተሰጠ ጊዜ 50' ደቂቃ**

**አጠቃላይ መመሪያ**

ውድ ተማሪዎች የዚህ ፈተና ዋና አላማ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት በማሳደግ ረገድ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ለታሰበው ጥናት መረጃ ለማሰባሰብ ነው። አንድ ምንባብ ቀርቧል፤ ከምንባቡ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ስለዚህ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎቹ መልስ ነው የምትለውን (ይውን) በመልስ መስጫ በተሰጠው ቦታ አስቀምጥ (ጪ) ፡፡

## ንባብ

## ወላጆችን ማክበር

እንደምን አመሻችሁ ልጆች? አሁን ሰብሰብ ያላችሁት እንደተለመደው ተረት ለማዳመጥ ነው፡፡ ሁላችሁም የታዘዛችሁትን ስራ ጨርሳችኃል? መቼስ አያቶች በሽምግልና እድሜያችን የሰጡትን እያበላን፣ ለእናንተ ተረት መንገርና መምከር ነው ስራችን እንዲሰማችሁ ስብሰብ በሉ! እንግዲህ ዛሬ የምነግራችሁ ተረት ሳይሆን አንድ አባት የነገሩኝን እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ እየተከታተላችሁኝ ነው? እማዶ ቁጭ ያልከው ታዳምጠኛለህ? ጥሩ!

ታዲያ እየሁላችሁ አንድ ቀበጥ ልጅ የነበራት አንዲት እናት ነበረች፡ ፊቷ በእሳት የተለበለበ ነበር፡፡ የሚያዩዋት ሁሉ ይገረማሉ፤ አንዳንዶችም ይሸሿታል፡፡ በተለይ ልጇ በእናቱ የተጨማደደና የጠቆረ ፊት ስለየሚያፍር አብሯት መታየትም ሆነ ወደ ትምርት ቤት አብራው እንድትሄድ አይፈልግም ነበር፡፡ ለተወሰኑ ጓደኞቹ "እናቴ ሞታለች" ለሌሎቹ ደግሞ "እናቴ ውጪ ሀገር ሄዳለች" እያለ ይዋሻቸው ነበር፡፡ እያዳመጣችሁኝ ነው? በጄ! እድሜው እየጨመረ በትምህርት እየገፋ መጣ በመጨረሻም ከኮሌጅ ተመርቆ ጥሩ ስራ ያዘ ከጥሩ ደረጃም ላይ በመድረስ በሰዎች ዘንድ ክብር አገኘ ፡፡ ‹‹ነገር ግን ጓደኞቹንም ሆነ ሌሎቹን ወዳጆቹን ወደ ቤት ለማምጣት አይደፍርም ነበር፡፡ በድንገት ወደ ቤቱ ለመጡትም ቢሆን እናቱን ሰራተኛዬ ናት›› እያለ ያስተዋውቃቸዋል፡፡ አንድ ቀን እናቱ ልታግረው ጠራችው፡፡

እያንጎራጎረ መጣ ከፊት ለፊቱ ተቀመጠች "ለመሆኑ ለምን እንደዚህ እንደሆንኩ ታውቃለህ?" አለችው እሱም "ስትፈጠሪ እንዲህ የሆንሽ ይመስለኛል" አላት "አይደለም" አለችው፡፡ ከዚያም አንድ ፎቶ አወጣችና አሳየችው እጅግ የተዋበች ለግላጋ ወጣት ማናት?" ብሎ ሲጠይቃት "ከጀርባው ተመልከተው" ስትል መለሰችለት ጀርባውን ገልብጦ ሲመለከተው የእናቱ ስም ተፅፏል እናቱ ከ30ዓመት በፊት ከትምህርት ቤት ጎደኞቿ ጋር የተነሳችው ፎቶ ነበር፡፡ «አላምንም» አላት ደንግጦ እንዲያረጋግጥ በማለት ሌሎች ፎቶዎችን ጨመረችለት "ለምን እንዲህ ሆንሽ?" በማለት አፍጥጦ ጠየቃት፡፡

"አንድ ቀን አንተ የአስር ወር ህፃን እያለህ እንቅልፍ ወስዶህ አልጋ ላይ ተኝተህ ነበር፡፡ እኔ የዳቦ ስንዴ ፀሀይ ላይ ላሰጣ ከቤት ውጪ ነበርኩ፡፡ አባትህም እቤት አልነበረም ስንዴውን አስጥቼ ዘወር ስል ቤታችን በእሳት ተያይዟል፡፡ ኡ.... !ኡ...! ኡ....! እያልኩ ጮህኩ፤ የሰፈራችን ሰዎች በሙሉ ተሰበሰቡ ነገር ግን እሳቱን ለማጥፋት ከመሯሯጥ በስተቀር አንተን ለማዳን ያሰቡ አልነበሩም፡፡" "እኔ ግን በእሳቱ መካከል ቀልቤን ስጥቼ ገባሁ፡፡ አንተን በብርድልብስ ሸፍኜ አምላኬን እየተማፀንኩ ይዤህ ወጣሁ፡፡ ልብሴ በእሳት በመያያዙ ከፊሉ አካሌ ተጎድቶ ነበር፡፡ የአንተ እሳት እኔ ተቃጠልኩልህ አየህ ልጄ! የአንተቃጠሎ ለእኔ ሆነ፤ የእኔ ጤናና ውበት ደግሞ ለአንተ ሆነ አለችው፡፡

በዚህም ጊዜ ልጁ ራሱን ይዞ በመጮህ ከእናቱ እግር ስር ወድቆ ይቅር እንድትለው ተማፀናት። አያችሁ ልጆች ወላጆቻችሁ እናንተን ሲያሳድጉ ብዙ ለፍተውና ደክመው ነው። እስኪ ከዚህ ከነገርኳችሁ ታሪክ ምን ተረዳችሁ? አዎ! ጥሩ ብላችኃል ወላጆች ቢከሱ፣ ቢጎሳቆሉ፣ አካላቸው ቢጎዳ ሊናቁና ሊገለሉ አይገባም። ወላጆችን ማክበርና መንከባከብ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ስለዚህ እናንተ ወላጆቻችሁን አክብሩ እሺ! በተረፈ ነገ ደግሞ ሌላ ተረት እተርትላችኃለሁ አሁን ስለመሸ ወደ ቤት እንግባና ራታችንን እንብላ ።

ምንጭ ፦ (ከዳንኤል እይታዎች 2005ዓ.ም ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

**ትዕዛዝ አንድ ፡- ሀ. ወላጆችን ማክበር በሚለው ምንባብ መሰረት ትክክል የሆነው "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት በፅሁፍ መልስ /ሺ/ ( 30% )**

1. እቤቱ በእሳት ሲያያዝ ቀበጡ ልጅ የአምስት ወር ህጻን ነበር።
2. በሽምግልና ወቅት አያቶች ተረት ይነግሩናል።
3. ወላጆች ልጆችን ለማሳደግ ሲሉ እራሳቸውን አሳልፈው አይሰጡም።
4. ቀበጡ ልጅ የእናቱ ፊት የተለበለበው በተፈጥሮ ይመስለው ነበር።
5. የቀበጡ እናት ልብስ ስታጥብ ነበር እቤቱ በእሳት የተያያዘው ።
6. ሰዎች እሳቱን ለማጥፋት የሚሯሯጡት ልጁን ለማትረፍ አስበው ነው ።
7. ወላጆች ቢከሱ፣ ቢጎሳቆሉ፣ አካላቸው ቢጎዳ ሊናቁና ሊገለሉ አይገባም።
8. ቀበጡ ልጅ የእናቱ ፊት በእሳት በመለብለቡ እፍረት አይሰማውም ነበር።
9. ቀበጡ ልጅ ፍቶዎችን እና ታሪኩን ከተረዳ በኋላ ነበር በሰራው ስራ የተፀፀተው ።
10. ወላጆችንና ታላላቆችን ማክበር ተገቢ ነው ።

**ትዕዛዝ ሁለት፡- ለ. "ወላጆችን ማክበር" በሚለው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ / ሺ / ። (30%)**

1. ቀበጡ ልጅ እናቴ ሞታለች የሚለው ለምን ነበር?
2. የቀበጡ ልጅ እናት የደረሰባት አደጋ ምን ነበር?
3. ቀበጡን ልጅ እናቱ በእሳት እንዳይቃጠል ያዳነችው እንዴት ነበር?
4. የቀበጡ ልጅ እናት የአንተን ቃጠሎ እኔ ተቃጠልኩልህ ስትል ምን ለማለት ፈልጋ ነበር?
5. ቤቱ በእሳት ሲያያዝ የቀበጡ ልጅ እናት የት ነበረች?
6. ቀበጡ ልጅ ጓደኞቹንም ሆነ ወዳጆቹን ወደ ቤት ያመጣቸው ነበር?
7. ጎረቤቶቹ እሳቱን ለማጥፋት ሲሯሯጡ ልጁ እቤት ውስጥ መኖሩን ያውቁ ነበር?
8. ወላጆችን ማክበር ለምን ይጠቅማ?
9. ቀበጡ ልጅ እናቱን ይቅርታ የጠየቀው ለምንድን ነው?

10. ከቀበጡ ልጅ ታሪክ ምን ተማራችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ሶስት ፡- "ወላጆችን ማክበር" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት እና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን አዛምድ / ጂ / ( 20% )**

| ‹‹ ሀ ›› | ‹‹ ለ ›› |
|---|---|
| 1. ተጨማደደ | ሀ. መከለል / መጋረድ / |
| 2. መማፀን | ለ. ተቀጣጠለ |
| 3. መልፋት | ሐ. ግማሹ |
| 4. ማግለል | መ. ማዳን |
| 5. ውበት | ሠ. የተኮማተረ |
| 6. ማትረፍ | ረ. መለመን |
| 7. መሸፈን | ሰ. መራቅ |
| 8. ተያያዘ | ሸ. ቁንጅና |
| 9. አደጋ | ቀ. ጉዳት |
| 10.ከፊሉ | በ. መልፋት |

**ትዕዛዝ አራት፡- ‹‹ ወላጆችን መክበር ›› በሚለው ምንባብ መሰረት በአረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ፃፊ / ፍ / (5 %)**

1. የቀበጡ ልጅ እናት ፊቷ በእሳት <u>የተለበለበ</u> ነበር፡፡
2. እኔ ግን በእሳቱ መካከል <u>ቀልቤን ስቼ</u> ገባሁ፡፡
3. አንተን በብርድልብስ ሸፍኜ አምላኬን <u>እየተማፀንኩ</u> ይገፔህ ወጣሁ፡፡
4. ወላጆቻችሁ እናንተን ሲያሳድጉ ብዙ <u>ለፍተው</u> ነው ፡፡
5. እናቱን የሚያዩዋት ሁሉ <u>ይገረሙ</u> ነበር ፡፡

**ትዕዛዝ አምስት ፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አያያዥ ቃላት በመምረጥ ባዶቦታውን አሟላ/ዪ/(5 %)**

1. አስፈላጊውን ዝግጅት አድረጌያለሁ ------------------ ፈተናውን በድል አጠናቅቃለሁ፡፡

   ሀ .ነገርግን   ለ . ወይም   ሐ . ሆነ   መ . ስለዚህ

2. በሚቀጥለው ሳምንት ------------- አስራምስት ቀን ወደ ላሊበላ መሄዴ አይቀርም ፡፡

   ሀ . ቢሆንም   ለ . ወይም   ሐ . ስለዚህ   መ . ደግሞ

3. ማስርሻ ኳስ ተጫዋች ሲሆን ፋጡማ -------------ሯጭ ናት ፡፡

ሀ . ደግሞ ለ . ስለሆነም ሐ . ወይም መ . ነገርግን

4. ሴቶችም ---------------- ወንዶች እኩል መብት አላቸው ፡፡

ሀ. ቢሆንም ለ . ነገርግን ሐ . ሆኑ መ . ስለሆነም

5. ነገ --------- ተነገወዲያ የሩጫ ውድድር አለብን ፡፡

ሀ . ሆነም ለ . ወይም ሐ . ስለዚህ መ . ቢሆንም

## አባሪ ለ

## ድህረ ትምህርት ፈተና

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ጋዜጠኝነት እና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## አማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ኮድ_____________

ለ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ድህረ ትምህርት ፈተና (100%)'

የፈተናው መነሻ ሰዓት 3፡00

ለፈተናው የተሰጠው የጊዜ ገደብ 1፡30

### አጠቃላይ መመሪያ

ውድ ተማሪዎች የዚህ ፈተና ዋና አላማ ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያለው ሚና ለመፈተሽ ለታሰበው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፣ ጥያቄዎቹ በምንባቡ መሰረት የሚመለሱ ሆነው አምስት ንኡሳን ክፍሎ አሏቸው፡፡ አንድ ምንባብ ቀርቧል ከምንባቡ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ስለዚህ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎች መልስ ነው የምትለውን/ይውን/ በመልስ መስጫ በተሰጠው ቦታ ፃፍ /ፊ /፡፡

## ምንባብ

የአሸንዳ ጭፈራ ከነሀሴ 16 እስከ 19 ባሉ ሶስት ተከታታይ ቀናት ይከበራል። በአሉ በዋንኛነት የልጃገረዶች በአል ነው። ትዳር የመሰረተች በአሸንዳ ጭፈራ አትሳተፍም። በዓሉ የመስክ በዓል በመሆኑ የአሸንዳ ሴቶች የትዋላችሁ ተብለው አይጠየቁም። የትዋላችሁ ተብለው የማይጠየቁበት ምክንያት የነፃነት ቀናቸው ነው። በአሸንዳ ፍቅራቸውን የሚገልፁበት፣ መንደሮቻቸውን የሚያዳምቁበት፣ አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን የሚያከብሩት ህዝባዊ በዓል ነው። ለበዓሉ ውሱን ቀናቶች ሲቀሩ ሴቶች ቡድን ይመሰርታሉ። ቡድኑ በአብሮ አደግ ልጃገረዶች የአንድ መንደር ልጆች ይዋቀራል። እነዚህ አብሮአደጎችም ሴራ-ሚዜ ይባላሉ። ቡድኑም የቡድን መሪ፣ ዘፈን አውጪ፣ ከበሮ መቺ በሚል ይደራጃል። የቡድን መሪዋ ዋና ተግባር ቡድኑን በተገቢው መምራት፣ ዘፈን የሚያወጡ፣ ከበሮ የሚመቱ መደልደል፣ ከየቤቱ የሚሰጡ ስጦታዎችን የመያዝ ስራዎችን ታከናውናለች። ሴራ-ሚዜዎች የሚወጡ ዘፈኖችን ይቀበላሉ። የቡድኑ አባላት በዓሉ ሊጀመር ውስን ቀናቶች ሲቀሩ ለበአሉ ድምቀት የሚሰጡ የሴት መጋጌጫዎችን እንደ ኩል፣ በዳሌያቸው የሚያስሩት አሸንድየ በመቁረጥና እንሶስላ በማዘጋጀት ዝግጅቱ ይጀመራል። በበዓሉ ቀንም ኮረዳዎቹ (አሳዲዎቹ) ፀጉራቸውን ቅቤ ተቀብተው እንሶስላቸውንሞቀው በበኩላቸው ደምቀው በአገር ባህል ልብሳቸው አሽብርቀው፣ በዳሌያቸው ዙሪያ አሸንዳ አስረው ከበሯቸውን እየመቱ በገላጣ ሜዳ ላይ ይሰበሰባሉ።

በበዓሉ መጀመሪያ ቀን በአቅራቢያቸው በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ለፈጣሪያቸው ምስጋና ያቀርባሉ። በመቀጠልም አምና የቡድን አባል የነበረች ነገር ግን ዘንድሮ ባላትዳር የሆነችው ጓደኛቸው ቤት በመሄድ የአሸንዳ ጭፈራቸውን ያሳያሉ። ጓደኛቸውን ያወድሷታል ፤ትዳሯ ያማረ ዘሯ የተባረከ እንዲሆን በዜማና በግጥማቸው ይመኙላታል። ሙሽራዋም ሚዜዎችዋም እደሚመጡ ስለምታውቅ ቀድማ የሚበላ ነገር ታዘጋጃለች። የአሸንዳ ቡድኑ ከሚዜዋ ቤት የጀመሩትን ጭፈራ በየቤቱ በመዞር ለህብረተሰቡ እንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸው በጭፈራቸው ያስተላልፋሉ። በምላሹምመለስተኛ ስጦታዎች ያገኛሉ። በአሉ ለሁለት ቀናት እየተዜመ ይከበራል ። የተለያዩ ስጦታዎች ይሰበስባሉ። ወንዝ ተሻግረው በየጎጡ ስለሚዞሩ ወንዶቹም ያጅቧቸዋል፤ ከጥቃትም ይጠብቋቸዋል። በሶስተኛው ቀንም የአሸንዳ ቡድኑ በአንድ ላይ በመሰባሰብ የጭፈራ ቀን ይከበራል። ጭፈራውም በወንዝ ዳር ባሉ አዳ(ዋርካ) ዛፍ ስር ይሆናል። በመጨረሻም ለከርሞ በሰላም እንዲያገናኛቸው ተመኝተው በአሉን በድምቀት ይሸኙታል።

**ምንጭ፡-** ክብሮም (2005) የራያ ህዝብ ባህልና ታሪክ ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የቀረበ።

**ትዕዛዝ አንድ ፦ ‹‹ የአሸንዳፐ ጭፈራ በሚለው ምንባብ መሰረት ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልስ / ሺ / (30 %)**

1. ሴራ - ሚዜዎች የአንድ አገር ልጆች ናቸው ።
2. የአሸንዳ በዓል የቡድን መሪዋ ተግባር ዘፈን መቀበል ነው ።
3. የአሸንዳ በዓል የሚከበርበት ቀን ከሐምሌ 16 — 19 ነው ።
4. ለበዓሉ ውሱን ቀን ሲቀረው ሴቶች ቡድን ይመሰርታሉ ።
5. በሶስተኛው ቀን በዓሉ የሚከበረው ወንዝ ዳር ኦዳ (ዋርካ) ዛፍ ስር ነው ።
6. የአሸንዳ በዓል ተሳታፊዎች አሸንድዬን የሚያስሩት ዳሌያቸው ላይ ነው ።
7. በአሉ የመስክ በአል በመሆኑ ሴቶች የት ዋላችሁ ተብለው የማይጠየቁበት ምክንያት ነፃነት ቀናቸው ነው።
8. በበአሉ ዕለት ኮረዳዎቹ ፀጉራቸውን ቅቤ ይቀባሉ።
9. በበአሉ ዕለት ኮረዳዎቹ ፀጉራቸውን ቅቤ ይቀባሉ።
10. ትዳር የመሰረተች ጓደኛቸው በአሸንዳ ጭፈራ አትሳተፍም።

**ትዕዛዝ ሁለት፡- "የአሸንዳ ጭፈራ" በሚለው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ መልሺ /ስ / (30%)**

1. በአሸንዳ በአል በዋናነት የሚሳተፉት እነማናቸው?
2. የአሸንዳ በአል ለስንት ቀናት ይከበራል?
3. የምንባቡ መልዕክት ምንን ያስተምራል?
4. በበዓሉ ዕለት የአሸንዳ ሴቶች የት ዋላችሁ ተብለው የማይጠየቁትበት ምክንያት ምን ነበር?
5. ባለትዳሯ ጓደኛቸው ሚዜዎቿ እንደሚመጡ አውቃ ምን ታዘጋጃለች?
6. የአሸንዳ ቡድኑ በአንድ ላይ በመሰባሰብ የጭፈራ ቀን የሚያክከብሩት በስንተኛ ቀንነው?
7. ሴራ -- ሚዜዎች ተግባር ምንድነው?
8. ሴቶች ወንዝ ተሽግረው በየጎጡ ሲዞሩ የሚያጅቧቸው እነማን ናቸው?
9 . ለበዓሉ ድምቀት የሚውሉ የሴት መጋጌጫዎች ምን ምን ናቸው?
10. ከየቤቱ የሚሰጡ ስጦታዎችን የሚይዘው ማነው?

**ትዕዛዝ ሶስት፡- የሚከተሉትን ከምንባቡ ለወጡ በ"ሀ" ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት እና ሀረጋት ከ "ለ" ክፍል ተመሳሳያቸውን አዛምድ /ጂ/ (30%)**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| _________ 1. መጋጌጫ | ሀ. በሚቀጥለው አመት |
| _________ 2. መስጠት | ለ. መጠበቅ |
| _________ 3. ማከናወን | ሐ. አምረው |
| _________ 4. ሴራ ሚዜ | መ. ኮረዳ |
| _________ 5. ለከርሞ | ሠ. መለገስ |
| _________ 6. መንደር | ረ. ማጠናቀቅ |
| _________ 7. አሳዲ | ሰ. መዋቢያ |
| _________ 8. አሽብርቀው | ሸ. አብሮ አደግ ልጃገረዶች |
| _________ 9. አምና | ቀ. ባለፈው አመት |
| _________ 10. መከላከል | በ. ሰፈር |

**ትዕዛዝ አራት ፦የሚከተሉትን የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍቺያቸውን ፃፍ /ፊ / (5%)**

1. ትዳር የመሰረተች ጓደኛቸው በአሸንዳ ጭፈራ አትሳተፍም፡፡
2 . ሴራ - ሚዜዎች የሚወጡ ዘፈኖችን ይቀበላሉ ፡፡
3. በአሸንዳ በዓል የወንዶች ሚና ሴቶቹን ማጀብና ከጥቃት መከላከል ነው ፡፡
4. በሶስተኛው ቀን ጭፈራው የሚከናወንበት ቀን ነው ፡፡
5. የበዓሉ የመጀመሪያ ቀን የሚከበርበት ስፍራ ቤተክርስቲያንነው ፡፡

**ትዕዛዝ አምስት ፦የሚከተሉትን ጥያቄዎች አያያዥ ቃላት በመምረጥ ባዶቦታውን አሟላ /ዪ/ (5%)**

1. አቤልጥናት በደንብ ያጠናል ------------ ጥሩ ውጤት አላመጣም ፡፡
   ሀ . ስለዚህ ለ . ምክንያቱም ሐ . ነገርግን መ . ወይም
2. ማሚት ቤተሰቧን ትወዳለች -------------- በስራ ታግዛቸዋለች ፡፡
   ሀ.ወይም ለ . ግን ሐ . ስለዚህ መ. ይሁን እንጂ
3. ሰናይ -------- ሐሊማ ዘወትር ኳስ ይጫወታሉ ፡፡
   ሀ .ይሁን እንጂ ለ . እና ሐ . ሆኖም መ . ደግሞ
4. ብሩክ እራቱን በልቷል -------------------አልተስማማውም ፡፡
   ሀ . ነገርግን ለ . ስለዚህ ሐ .ምክንያቱም መ . እንዲሁም

5. መክሊት ገበያ ሂጂና ሙዝ ------------ ቲማቲም ገዝተሸ ነይ

ሀ. ወይም ለ. ሆኖም ሐ. ስለሆነም መ. ቢሆንም

## አባሪ ሐ

**ማስተማሪያ ፅሁፍ**

ስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያለው ሚና ለመፈተሽ በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት መረጃን እንዲያስገኝ ለ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት በሳምንት ለሁለት ቀን ጠቅላላ የትምህርት ሰዓት 14 ክፍለ ጊዜያት ፡፡


**ትምህርት ሁለት**

የትምህርት ርዕሶች፡- የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ፣ የፐላስቲክ ተፅዕኖ፣ በድሉና ውቢቷ ኢትዮጵያ፣ የጥንካሬ ተምሳሌት እና የስራ ክፍፍል በርዕስነት የቀረቡ ናቸው፡፡ ምንባቡን አንብበው ምንባቡና ስዕሉ ያላቸውን ዝምድና መለየት፣ የምንባቡን ሀሳብ በማስታወስ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን መለየት የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ ፡፡

**ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ** 2፡00

- የትምህርቱ አላማ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች ስዕልና ምንባቡ ያላቸውን ዝምድና ይናገራሉ፡፡
- የምንባቡን ሀሳብ በማስታወስ ለጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡















ቀይ ቀበሮ



ኒያላ



የምኒልክ ድኩላ



**ንባብ**

**የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ**

**ቅድመ ንባብ**

*ሀ. ስዕሉ ስለፓርኩ ምን ይገልፃል?*

*ለ. ፓርክ ጎብኝታችሁ ታውቃላችሁ ከማን? ጋር?*

*ሐ. ካያችሁት ስዕል በተጨማሪ ምን ምን ይገኛል?*

በኢትዮጵያ የሚገኙት ፓርኮች መካከል የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ አንዱ ነው፡፡ ፓርኩ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በባሌ ዞን የሚገኝ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ምስራቅ 400ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሲገኝ ከሻሸመኔ ከተማ ደግሞ በ150ኪሎ ሜትር በስተምስራቅ ይገኛል፡፡ የባሌ ብሔራዊ ፓርክ 2220ካሬ ሜትር ስፋት እንዳለው የሚገመት ሲሆን እ.አ.አ በ1970 በፓርክነት ተከለለ፡፡

በአለም ቅርስነት የተመዘገበው የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ በቀዝቃዛ የአየር ንብረት ይታወቃል፡፡ ፓርኩ ከባህር ወለል በላይ ከ1442-4377ሜትር ከፍታ አለው፡፡ የዝናብ መጠኑ በአመት 650-1300 ሚሊ ሜትር እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ አስገራሚ መልከዓምድራዊ ገፅታዎች አሉት፡፡ ተራራዎቹ እንደሀውልት ተጠርበው የወጡና እንደመደብ የተደለደሉ ኮረብታዎች ግዙፍና እንደሰንሰለት የተያያዙ የሚመስሉ ውብና አስገራሚ ቅርስ ያላቸው የመሬት ገፅታዎችና ጥቅጥቅ ያለ ደን በባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ መለያዎች ናቸው፡፡

*ሀ. የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ከአዲስ አበባ ምን ያህል ርቀት አለው?*

*ለ. በባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ የሚገኙ እንስሳት መካከል የምታውቋቸውን ጥቀሱ?*

በባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ድርብ የተፈጥሮ ትዕይንት የሚታይበት ስፍራ ነው፡፡ በፓርኩ ውስጥ በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኙ 20 አጥቢ እንስሳት ውስጥ 5ቱ በፓርኩ ውስጥ

ይገኛሉ። በተጨማሪም በአገራችን ከተመዘገቡት 663 የአዕዋፍ ዝርያዎች መካከል 16 የሚሆኑት በባሌ ብሔራዊ ፓርክ ይገኛሉ።

የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጎብኝዎችን የሚስቡና የፓርኩ መታወቂያ ከሆኑት የዱር እንስሳት መካከል ቀይ ቀበሮ፣ የደጋ አጋዘን፣ ከርከሮ፣ኒያላና የሚኒሊክ ድኩላ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም በፓርኩ ውስጥ ኮሶና ጥድ የመሳሰሉ አገር በቀል ዛፎችና ለተለያዩ በሽታዎች መፈወሻ፣ የባህላዊ መድሀኒት መቀመሚያነት የሚያገለግሉ ዕፅዋት ይገኛሉ። በአጠቃላይ የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ በአስገራሚ መልክአምድራዊ ገፅታውና በእንስሳት ስብስቡ፣ ጥቅጥቅ ባለ ደኑ ይታወቃል። በዚህም በርካታ የውጭና የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ስለሚጎበኙት ለሀገሪቱ ከፍተኛ ገቢ በማስገኘት ላይ ይገኛል።

ምንጭ ፦ የቀድሞ የሰባተኛ ክፍል ከመምህሩ መምሪያ ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ የተወሰደ ።

**ሀ. የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ በሚለው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በፅሁፍ መልሱ።**

1. ፓርኩ በፓርክነት የተከለለው በስንት አመተ ምህረት ነው?
2. የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጎብኝዎችን የሚስቡና የፓርኩ የመታወቂያ ከሆኑ የዱር እንስሳት እነማን ናቸው?
3. የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ በምን በምኑ ይታወቃል?
4. በፓርኩ ውስጥ የምንና የምን አገር በቀል ዛፎች ይገኛሉ?
5. የፓርኩ የዝናብ መጠን ምን ያህል ነው?

**ለ. ባነበባችሁት ምንባብ መሠረት በ ‹‹ ሀ ›› ክፍል ለተዘረዘሩት ከ ‹‹ ለ ›› ክፍል መገለጫቸው ጋር አዛምድ / ጂ /**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ________ 1. ፓርኩ ከሻሸመኔ በስተምስራቅ | ሀ. 5ቱ በፓርክ ውስጥ ይገኛሉ። |
| ________ 2. የባሌ ብሄራዊ ፓርክ ስፋት በግምት | ለ.አገር በቀል ዛፎች ይገኙበታል። |
| ________ 3. የፓርኩ መገኛ ቦታ | ሐ.2220 ካሬ ሜትር ይገመታል። |
| ________ 4. በአለም ቅርስነት የተመዘገበው | መ. 16ቱ በፓርኩ ውስጥ ይገኛል። |
| ________ 5. በፓርኩ ውስጥ በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኙ 20 አጥቢዎች ውስጥ | ሠ. 150 ኪሎ ሜትር |
| ________ 6. በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኙ 663 የአዕዋፍ ዝርያዎች መካከል | ረ. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በባሌ ዞን |

_________ 7. ለባህላዊ መድሀኒት መቀመሚያነት የሚያገለግሉ ሰ. በቀዝቃዛ የአየር ንብረቱ

**ሐ. ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ፃፍ/ፊ/**

1. የሚስቡ
2. መፈወሻ
3. ስፍራ
4. ይጠቁማሉ
5. አስገራሚ





**ንባብ**

**የፕላስቲክ ተፅዕኖ**

**ቅድመ ንባብ**

*ሀ. የፕላስቲክ ተፅዕኖ የሚለው ምንባብ ርዕስ እና ስዕል ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኋል?*

*ለ. እናንተ ፕላስቲክ ተጠቅማችሁ የት ትጥሉታላችሁ?*

*ሐ. ተፅዕኖ ማለት ምን ማለት ነው?*

*መ. ፕላስቲክ መጠቀም ምን አይነት ጥቅም አለው? ጉዳቱስ ምንድን ነው?*

ፕላስቲክ አካባቢን ይበክላል፡፡ ፕላስቲክ አካባቢን የሚበክለው እኛ ተገልጋዮች የተጠቀምንባቸው የፕላስቲክ ምርቶች በደንብና በስርዓት ባለመጠበቃችን ሲሆን፣ የተጠቀምንባቸውን የፕላስቲክ ውድቅዳቂዎችን በየቦታው በመወርወር የሚከሰት ብክለት ነው፡፡ ምክንያቱም የሚጠቀመው ህብረተሰብ በአካባቢ ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ግንዛቤ ስለሌለው ነው፡፡

*ሀ. ፕላስቲክ አካባቢን የሚበክለው እንዴት ነው?*

*ለ. የፕላስቲክ ውጤት ተፅዕኖ ምን ሊሆን ይችላል?*

*ሐ. የፕላስቲክ ውጤት ተፅዕኖን እንዴት መከላከል ችንችላለን?*

የፕላስቲክ ውጤቶ እንደ እፅዋትና ሌሎች ቆሻሻዎች በቀላሉ አይበሰብሱም፡፡ በተለይም ውፍረታቸው ከ0ነጥብ 3 ሚሊ ሜትር ዲያሜትር በታች የሆኑ ፔስታሎች በቀላሉ ስለሚበታተኑ አትክልትና እህል በሚበዛባቸው ማሳዎች ላይ ካረፉ በምርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኗቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም አፈር ውስጥ ሲገቡ በቀላሉ፣ ስለማይበሰብሱ ችግኞችና እፅዋት አየር፣ ምግብና ውሀ የሚያገኙት በስሮቻቸው አማካኝነት ስለሆነ ዝውውርና ስርጭቱን ይከላከላሉ፡፡ ይህ አንደኛው ተፅዕኖ ሲሆን፣ ሁለተኛው ቀላል ስለሆኑ በአየርና በንፋስ ስለሚበታተኑ አካባቢን ያቆሽሻሉ፣ የእይታ ብክለት ያስከትላሉ፣ ቆሻሻ

እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ ሶስተኛው የፕላስቲክ ውጤቶች ሲቃጠሉ አየርን ይበክላሉ፡፡ ከጭሱ ጋር የሚበከል ‹‹ ዳይኦክሲ ›› የሚባለው ኬሚካል ደግሞ ካንሰር ያመጣል፡፡ ስለሆነም የፕላስቲክ ውጤቶችን ለማስወገድ ማቃጠልን ባንጠቀም መልካም ነው፡፡ በአብዛኛው እናቶች ከሰል ለማያያዝ ፔስታልን ጨምሮ ሌሎች የፕላስቲክ ውጤቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ትክክል ያለመሆኑን ለማህበረሰቡ ማስገንዘብ አለብን፡፡

የፕላስቲክ ምርቶች ለአካባቢ ብክለት ዋና መንስኤ በመሆናቸው ችግሩን ለመከላከል ለመገበያያ የሚውል ፔስታል የሚተኩ ከወረቀትና ሌሎች በቀላሉ የሚበሰብሱ ቁሳቁሶችን ወደ ማምረት ቢገባና በፕላስቲክ ምርቶች ላይ እገዳ ተግባራዊ ቢደረግ ችግሩን ማስወገድ ይቻላል፡፡

**ምንጭ፡-** ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ቅፅ 29 ቁጥር 3296 ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የቀረበ፡፡

**ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች "የፕላስቲክ ተፅዕኖ" በሚለው ምንባብ መሰረት የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. የፕላስቲክ ውጤቶች ቢቃጠሉ አየርን አይበክሉም፡፡
2. እናቶች አብዛኛውን ጊዜ እሳት ለማቀጣጠል የሚጠቀሙት ባህርዛፎችና ወረቀቶችን ብቻ ነው፡፡
3. ፕላስቲክ አካባቢን የሚበክለው እኛ ተጠቃሚዎች ውድቅዳቂዎችን በአግባቡ ሰብስበን ስለምናስቀምጥ ነው፡፡
4. የፕላውቲክ ውጤቶችን ለማስወገድ ማቃጠልን ብንጠቀም ጥሩ ነው፡፡
5. የፕላስቲክ ውጤቶች መተካት ያለብን በቀላሉ መበስበስ በሚችሉ ቁሳቁሶች ነው፡፡

**ለ. "የፕላስቲክ ተፅዕኖዎች" በሚለው ምንባብ መሰርት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. የፕላስቲክ ውጤቶች እንዳይመረቱ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
2. ፔስታሎች እህል በሚበዛባቸው ማሳዎች ላይ ካረፉ በምርት ውጤት ላይ እንዴት አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ?
3. ፀሀፊው የፕላስቲክ ውጤቶች የሚያሳድሩትን ተፅዕኖዎች በስንት ክፍሎች አቀረበ?
4. ስለ ፕላስቲክ ተፅዕኖዎች ማህበረሰቡን እንዴት ማስተማር ይቻላል፡፡
5. የፕላስቲክ ውጤቶችን በአብዛኛው ከሰል ለማያያዝ የሚጠቀሙት እነማናቸው?

**ሐ. ለሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ አገባባዊ ፍቻቸውን ምረጡ።**

1. የፕላስቲክ ማሳ ላይ ካረፈ በምርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አላቸው።

ሀ. ረባዳማ ቦታ ሐ. ዳገታማ ቦታ

ለ. የዕርሻ ቦታ መ. ቁልቁለታማ ቦታ

2. የፕላስቲክ አካባቢን የሚበክለው ድቅዳቂን በየቦታው በመወርወር ነው።

ሀ. በመሰብሰብ ሐ. በመክተት

ለ. በመጨመር መ. በመጣል

3. የፕላስቲክ ውጤቶች ቀላል ስለሆኑ በንፋስና በአየር ስለሚበታተኑ አካባቢን ያቆሽሻሉ።

ሀ. ያስውባሉ ሐ. ይበክላሉ

ለ. ያሳምራሉ መ. ያስጌጣሉ

4. ፕላስቲክ ምርቶች ላይ እገዳ ተግባራዊ ቢደረግ ችግሩን ለማስወገድ ይቻላል።

ሀ. ለመቅረፍ ሐ. ለመቁረጥ

ለ. ለመላጥ መ. ለማቆየት

5. ፕላስቲክ አካባቢን የሚበክለው እኛ ተገልጋዮች በደንብና በስርዓት ባለመጠበቃችን ነው።

ሀ . ተፈናቃዮች ሐ . ተጎጂዎች

ለ . ተጠቃሚዎች መ . ተወዳጆች







**ንባብ**

**በድሉና ውቢቷ ኢትዮጵያ**

**ቅድመ ንባብ**

ሀ. “በድሉና ውቢቷ ኢትዮጵያ” የሚለው የምንባብ ርዕስ ስለምን ጉዳይ የሚያነሳ ይመስላችኃል?

ለ. ከላይ የምትመለከቱት ስዕልና ርዕሱ ምን ግንኙነት አላቸው፡፡

በድሉ ከአባቱ ከአቶ በረከትና ከእናቱ ከወይዘሮ ፍቅርአዲስ የተወለደ የአስራ አምስት አመት ወጣት ነው፡፡ በትምህርቱ ጎበዝና በስነምግበሩ የተመሰገነ ልጅ በመሆኑ ሁሉም የሰፈሩ ልጆችና ነዋሪዎች ይወዱት ነበር፡፡ ካሌብ ከሚባል በሌላ ትምህርት ቤት ከሚማር ልጅ ጋር ጓደኝነት ከጀመረ ወዲህ ግን ፀባዩ ቀስ በቀስ እየተቀየረ መጣ፡፡ አንድ ቀን ካሌብ በድሉን ጠራውና አሜሪካ አገር የሚኖሩ ወንድሞች እንዳሉትና ስማቸውም ቦቢ እና ሮኪ እንደሚባሉና ፎቶ ግራፋቸውንም አሳየው በዱሉ የካሌብ ወንድሞችን ፀጉር አቆራረጥ ካየ በኃላ ፀጉሩን እንደነሱ ማስቆረጥ ፈልጎ በሚቀጥለው ቀን መሀሉን ብቻ አስቀርቶ ዙሪያውን አስላጨውና ፀጉሩን እሳት የበላው የጭድ ክምር አስመሰለው፡፡

ወላጆቹ ይህን ሲያዩ እጅና እግሩን ይዘው ሙሉ በሙሉ ፀጉሩን ላጩትና ቅባት ቀቡለት፡፡ በዚህም አላበቃም ሲያድግለት አንዴ ቢያጆ አንዳንዴ የቆመ ሰፌድ አስመስሎ ባላቶኒ ነኝ እያለ እንዲሁም ከወላጆቹ ተደብቆ ሱሪውን ከመቀመጫው ስር ለጥፎ ራቁቱን እያሳየ መሄድ ጀመረ፡፡ ጓደኞቹም ምንድን ነው? ብለው ሲጠይቁት? ዝነጣ ነው፡፡ ዝነጣ አይገባችሁም እንዴ? በማለት ያሿፍባቸው ነበር፡፡

በድሉ ስሜን ቀይራችሁ ሮኪ በሉኝ አንዳንዴ ደግሞ አሜሪካ መሄድ እፈልጋለሁ፤ አሜሪካ ምድረ ገነት ስለሆነች እያለ ወላጆቹን አስቸገረ። ወላጆቹ በሚሰጣቸው መልሶች እጅግ ተገርመው በዚህ እድሜው አሜሪካንን ማምለክ መጀመሩ አሳዘናቸው። ከካሌብ እንደሚውል የተረዱት ወላጆቹ ስለአገሩ በደንብ እንዲያውቅ "ውቢቷ ኢትዮጵያና ታሪኳ" የሚል አዲስ መፅሀፍ ገዝተው ሰጡት።

በድሉ የኢትዮጵያን ስልጣኔ፣ የነፃነት ተጋድሎን፣ የተፈጥሮ ሀብቷን፣ የአስራ ሶስት ወር ፀጋ፣ ባለቤነቷን፣ የህዝቦቿን አስደናቂ ባህሎችና ሌሎች በርካታ አኩሪ ታሪኮቿን ከመፅሀፉ አነበበ።

ሀገሩ ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠርና፣ የራሷ ፊደል ያላት መሆኗን ብርቅዬዋን ሉሲን ለአለም ያበረከተች የሰው ዘር መገኛ መሆኗን፣ የአክሱም ስልጣኔ፣ ከስምንት መቶ አመታት በፊት የተገነባው የላሊበላ ቤተክርስቲያን ባለቤት መሆኗን አወቀ። የጣሊያንን ወራሪ ሰራዊት በጎራዴ አርበርብዳ ያባረረች፤ የአፍሪካውያን በሙሉ ታላቅ ኩራት የሆነውን የአድዋድል የተቀዳጀች አፍሪካዊት አገር መሆኗን በሚገባ ተረዳ።

ሀ. በድሉ ወደ አሜሪካ መሄድ የፈለገው ለምን ነበር?

ለ. በድሉ ወደ አሜሪካ የመሄድ ሀሳቡን የሚለውጥ ይመስላችኃል?

በድሉ የአገሩን ታሪክ በሚገባ ከተረዳ በኃላ ወደ አሜሪካ የመሰደድ ምኞቱን ናቀ። ኢትዮጵያን ባልሆነ ስም ለመጥራት የነበረው ከፍተኛ ጉጉት ሲያስታውስ አፈረ። የባህል ወረራ ምርኮኛ ሆኖ ሱሪውን ከመቀመጫው ስር እየለጠፈ የጓደኞቹ መሳለቂያ መሆኑ ቆጨው፤ የራሱን ውብ ሀገር ንቆ ስደተኝነትን በመምረጡ ተፀፀተ።

በድሉ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤመፅሀፍት እየገባ ስለአገሩ የተፃፉ ልዩ ልዩ የታሪክ መፅሀፍት በብዛት አነበበ። "ታላቅ ነበርን ታላቅም እንሆናለን" በሚለው አባባል ኢትዮጵያ ከድህነት ተላቃ ወደ ቀድሞ ታላቅነቷ መመለስ እንደምትችል የሚገልፅ ጥልቅ ትርጉም ያለው መሆኑን ተገነዘበ።

አገሩን ወደ ቀድሞ ታላቅነቷ ለመመለስ በትምህርቱ ከክፍሉ እንደኛ መውጣት ጀመረ። በድሉ ዩኒቨርስቲ ገብቶ በመሀንዲስነት በድግሪ ተመረቀና በተማረው ሙያ አገሩን ሊያገለግል በአባይ ግድብ ፕሮጀክት መሀንዲስነት ተቀጠረ።

የአባይ ግድብ በቤንሻንጉል ዞን በጉባ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋም መሆኑን ጠንቅቆ ስለተረዳ ቀን ከሌሊት ሳይል በቁጭትና በፅልህ በመስራቱ ለግድቡ መጠናቀቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ቻለ። በዚህም የተነሳ የስራ ባልደረቦቹ በአንደኛ ደረጃ መረጡት፤ የአመቱ ምርጥ ሰራተኛ ተብሎ ሜዳሊያና የዋንጫ ተሸላሚ ሆነ

**ምንጭ፡- ትክክል ገና (2014) የገበሬው በጎች ወይ ተሰወሩ? አስደናቂ ታሪክ እና ሌሎችም አስደሳች ተረቶች ለክፍል በደረጃው ተመጥኖ የተዘጋጀ።**

**ሀ. "በድሉና ውቢቷ ኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለትመልስ / ሺ /**

1. ለበድሉ መፅሐፍ ገዝተው የሰጡት መምህራኖች ናቸው ።
2. በድሉ የቀድሞ ፀባዩ የተቀየረው ጓደኛው ስለወንድሞቹ ከነገረውና ፎቶዎችን ካየበኋላ ነው ።
3. በድሉ በሰራው ስራ የተጸጸተው የራሱን ውብ ሀገር ንቆ ስደተኝነትን በመምረጡ ነው ።
4. በድሉ የአባይን ግድብ ሲሰራ የነበረው በዕልህና በቁጭት ነበር ።
5. ለኢትዮጵያዊያን የባህል ወረራ ምርኮኛ መሆን አያስፈልግም ።

**ለ. "በድሉና ውቢቷ ኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ/ሺ/**

1. በድሉ የድሮ ፀባዬ ለምን ተቀየረ?
2. በድሉ ወላጆቹን ምን አድርጉልኝ በማለት ያስቸግራቸው ነበር?
3. አስገራሚውን የኢትዮጵያ ታሪክ በዝርዝር ግለፁ?
4. በድሉ በሰራው ስራ ለምን ተፀፀተ?
5. ፅሁፉ ምን መልዕክት ያስተላልፋል?

**ሐ. "በድሉና ውቢቷ ኢትትዮጵያ በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሠረት በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በ "ለ" ክፍል አቻቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| _________1. ሞገደኛ | ሀ. ጓደኞቹ |
| _________2. መገረም | ለ. ተቆጨ |
| _________3. ተፀፀተ | ሐ. መደነቅ |
| _________4. ማገልገል | መ. ሀይለኛ |
| _________5. ባልደረቦቹ | ሠ. መጠቀም |

**መ. “በድሉና ውቢቷ ኢትዮጵያ” በሚለው ምንባብ መሰረት ከሰንጠረዥ በመምረጥ ባዶ ቦታውን ሙላ/ይ/**


| | |
|---|---|
| ቤሻንጉል/ጉባ/ | ዝነጣ |
| በረከት | በመሀንዲስነት |
| ቢያጆ ባላቶኒ | |

1. በድሉ ፀጉሩን የተላጨው __________________ እና _____________ለመምሰል ነው፡፡
2. የበድሉ አባት ስም __________________ ሲሆን የእናቱ ስም ደግሞ _________ ይባላል
3. የአባይ ግድብ የተገነባው በ__________________ክልል ሲሆን ቦታው _________________ ተብሎ ይጠራል፡፡
4. በድሉ ጓደኞቹ ምንድነው? ብለው ሲጠይቁት ________________ነው እያለ ያሾፍባቸዋል፡፡
5. በድሉ ዩኒቨርስቲ ገብቶ ___________________________ በድግሪ ተመረቀ፡፡

**ሠ . የሚከተሉትን ጥያቄዎች አያያዥ ቃላት ከሳጥኑ በመምረጥ ባዶ ቦታውን አሟሉ ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምክንያቱም | ይሁን እንጂ | ወይም | ነገር ግን | ስለዚህ |

1. ነገ ወደ ሀዋሳ መሄድ እፈልግ ነበር ----------------- ገንዘብ የለኝም ፡፡
2. አናናስ ----------------- አፕል ለጤና ተስማሚ ነው ፡፡
3. ሜላት ወንድሞቿን ትወዳቸዋለች ----------- ታስጠናቸዋለች ፡፡
4. ልጁን ደጋግሜ መከርኩት ----------------ሊሰማኝና ሊመለስ አልቻለም ፡፡
5. ኤርሚያስ ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ አልፏል ----------- በማጥናቱ ፡፡



## ምንባብ

## የጥንካሬ ተምሳሌት

እናት ያደገችባትን በደቡብ ወሎ የምትገኘውን የሳይት ወረዳ ለቃ የኮበለለችው በወላጆችዋ ምክንያት ያለፍላጎታ ገና በለጋ እድሜ በአካባቢው ባህል መሰረት ስለዳሯት ነበር፡፡ ከባለቤቷ ሙሉነህ ጋር በእድሜ አቻ አልነበሩም፡፡ በመሆኑም ለሱ ፍቅር አልነበራትም፤ ሁልጊዜ ይጨቃጨቃሉ፡፡ የንትርኩና የጭቅጭቁ መደጋገም አስመረራት፡፡

አንድ ቀን ከጎረቤቶቿ ጋር ወደ ገበያ እንደወጣች ወደቤቷ ሳትመለስ ቀረች፡፡ ከቤቷ ስትወጣ ለመሸጥ ከያዘቻት ቋጠሮ እህል በስተቀር በመቀነቷ ምንም ገንዘብ አልያዘችም፡፡ በየመንገዱ በሀሳብ ትባዝናለች፡፡ ገበያ እንደደረሰች የያዘችውን ሻጣ ገንዘብ ካገኘች በኃላ ከነጋዴዎች ጋር ለመጓዝ ወሰነች፡፡

ነጋዴዎቹ የሚሄዱት ወደ አዲስ አበባ ስለነበር እሷም ተቀላቅላ ስትሄድ አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ ሰው ድንገት ጠየቋትና ችግሯን ዘርዝራ ነገረቻቸው፡፡ እሳቸውም አዲስ አበባ እህታቸውጋ እንደሚያስቀምጧት ተስፋ ሰጧት ፡፡ተስፋዋን ሰንቃ አዲስ አበባ ከእህታቸው ጋር አገናኟት፡፡ እህትየውም የቤት ስራ እስክትለምድ አሰነባበቷት፤ ከዚያም ተያዥ በመሆን ከግለሰብ ቤት በሰራተኝነት አስቀጠሯት በሰበብ በአስባቡ ጭቅጭቅ ስለበዛበት አንድ ወር ሰርታ ለቃ ወጣች፤ ከዚያም በተለያዩ ቤቶች እየተቀጠረች ብዙ አስከፊ ባህሪያትን አስተዋለች፡፡

በመጨረሻም የተቀጠረችበት ቤት ግን ከሁሉም የተሻለ ነበር፡፡ ባለቤቶቹና ልጆቻቸው መልካም ቀረቤታ ነበራቸው፡፡ ስራዋን ጠንቅቃ በመስራቷና በታማኝነቷ ሁሉም ወደዷት ፡፡ ገንዘቧን በባንክ እንድትቆጥብ ሁኔታዎችን አመቻቹላት፡፡ የቤት ስራዋን እየሰራች ማታ

እንድትማር ፈቀዱላት አሰሪዎቿ በቤት ውስጥ ያስጠኗታል፡፡ የምታነበውም መፅሀፍ ይገዙላታል፡፡ ጠንክራ በማጥናቷም ከክፍል ወደ ክፍል በጥሩ ውጤት እያለፈች ስድስተኛ ክፍል ደረሰች ከወላጆቿ ጋርም ደብዳቤ በመፃፃፍ መገናኘት ጀመረች፡፡

አንድ ቀን ግን የእናኑን ህይወት የሚለውጥ ነገር ተፈጠረ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ ሰዎች ተሰብስበው ማስታወቂያ ያነባሉ፡፡ እሷም ተጠግታ ማንበብ ጀመረች፡፡ ማስታወቂያው ስልጠና ከተሰጣቸው በኃላ በአነስተኛና ጥቃቅን ተደራጅተው መስራት የሚፈልጉ ወጣቶችን የሚመለከት ነበር፡፡ የኮረኮሯትን ያህል ፈነደቀች እቤት ሀሳቧን ነገረቻቸው፡፡ እነሱም ሀሳቧን በመደገፍ ይበልጥ አበረታቷት፡፡

በሚቀጥለው ቀን ወደ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ኤጀንሲ በመሄድ ስልጠናውን ጀመረች፡፡ በስልጠናው ሂደት በርካታ ጓደኞች አፈራች፡፡ ከተወሰኑ ቀናት በኃላም ከጓደኖቿ ጋር በማህበር ተደራጀች፡፡ ከዚያም በዳቦ መጋገር እና መሸጥ ንግድ ስራ ለመሰማራት ተስማሙ፡፡

የንግድ ስራቸውን ለመጀመር በነፍስ ወከፍ ገንዘብ እያዋጡ መቆጠብ ጀመሩ፡፡ የተዋጣው ገንዘብ በቂ ባለመሆኑ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ኢጀንሲ የብድር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው ጥያቄ አቀረቡ፤ ብድሩ ተፈቀደላቸው፡፡ ከዚያም መጋገርና መሸጥ ጀመሩ፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብም ዳቦውን በገፍ በመግዛት አበረታቷቸው፡፡ ምርቱ እየጨመረ በመምጣቱ በተለያዩ ቦታዎች የማከፋፈያና የመሸጫ ሱቆች ከፈቱ፡፡ በዚህም ገበያቸው በማደጉና ትርፋቸው በመጨመሩ ሌላ ድርጅት ለመክፈት ተመካክረው አዋጭ ነው ያሉትን የብሎኬት ማምረቻ ከፈቱ፡፡ ሌሎች የስራ ዕድል በመክፈት አዳዲስ ሰራተኞችን ቀጠሩ፡፡ የዳቦ ቤቱና የብሎኬት ማምረቻው በአንድ ላይ ከፍተኛ ገቢ አስገኙላቸው ፡፡አባላቱ በስራቸው ተለወጡ፡፡ እናኑ ከተቀጣሪነት ወጥታ ቀጣሪ ሆነች፡፡ በጥንካሬዎቿ የኑሮዋና የህይወቷ አቅጣጫ ተለወጠ፡፡

**ምንጭ፡-የቀድሞ የሰባተኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የቀረበ፡፡**

## ሀ. “የጥንካሬ ተምሳሌት” በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ /5%/

1. እናኑ ያደገችበትን ቦታ ለቃ የኮበለለችው በማን ምክንያት ነው?
2. በስራ ውጤታማ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?
3. እናኑ ትዳር የመሰረተችው ምን ጊዜ ነበር?
4. እናኑ አዲስ አበባ ከማን ጋር ነው የሄደችው?
5. እነ እናኑ በመጀመሪያ የተሰማሩበት የንግድ ስራ ምን ነበር?

**ለ . በምንባቡ መሰረት በ “ሀ” ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳያቸውን ከ “ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምድ/ጂ/**

| | ‹‹ ሀ ›› | ‹‹ ለ ›› |
|---|---|---|
| ___________ | 1. መሄድ | ሀ. መገንዘብ |
| ___________ | 2. አቅጣጫ | ለ. በአጋጣሚ |
| ___________ | 3. አዋጭ | ሐ. መደሰት |
| ___________ | 4. ኮበለለች | መ. ይዛ |
| ___________ | 5. ተለወጠ | ሠ. ጠፋች |
| ___________ | 6. እያደገ | ረ. ከፍ እያለ |
| ___________ | 7. ሰንቃ | ሰ. አትራፊ |
| ___________ | 8. በድንገት | ሸ. መስመር |
| ___________ | 9. ማስተዋል | ቀ. መጓዝ |
| ___________ | 10. መፈንደቅ | በ. ተቀየረ |

**ሐ .በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ የተጓደሉትን አረፍተ ነገሮች በሳጥን ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት በመምረጥ አሟሉ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ትባዝናለች | ከተወሰኑ | ቀረቤታ |
| መደጋገም | አስከፊ | በነፍስወከፍ |

1. እናኑ በተለያዩ ቤቶች እየተቀጠረች ብዙ ___________ ባህሪያትን አስተናግዳለች፡፡
2. የንግድ ስራውን ለመጀመር ______________________ ገንዘብ እያዋጡ መቆጠብ ጀመሩ፡፡
3. ______________________ ቀናት ስልጠና በኃላም በርካታ ጓደኞች አፈራች፡፡
4. በየመንገዱ በሀሳብ ______________________ ፡፡
5. የንትርኩና የጭቅጭቁ ___________________ አስመረራት ፡፡
6. ልጆቹም ሆኑ ወላጆቹ ከእናቱ ጋር መልካም ___________________ ነበራቸው፡፡

መ . የሚከተሉትን ቃላት በማጥበቅና በማላላት የሚሰጡትን ትርጉም ፃፉ፡፡

| በማጥበቅ የሚሰጠው ትርጉም | በማላላት የሚሰጠው ትርጉም |
|---|---|
| 1. ሰጋ | |
| 2. ያነባል | |
| 3. ጥልቅ | |
| 4. አያት | |
| 5. ቀናት | |

ሠ .የሚከተሉትን ጥያቄዎች አያያዥ ቃላት ከሳጥኑ በመምረጥ ባዶቦታውን አሟሉ ፡፡

| | |
|---|---|
| ግን | ከዚያምበመጨረሻም |
| በመሆኑም | እና |


1. እናኑ ከጓደኞቿ ጋር ተደራጀች፤ ---------------- በዳቦ መጋገርና ንግድ ስራ ተሰማሩ ፡፡


2.ምርቱ እየጨመረ በመምጣቱ በተለያዩ ቦታዎች የማከፋፈያ ----------- መሸጫ ሱቆች ከፈቱ ፡፡

3.አባላቱ በስራቸው ተለወጡ ፤ --------------- እናኑ ከቀጣሪነት ወደ አሰሪነት ተለወጠች ፡፡


4.እናኑን ወላጆቿ ያለፍላጎቷ በለጋ ዕድሜ ስለዳሯትከባለቤቷ ጋር በዕድሜ አቻ አልነበሩም ------------ ለሱ ፍቅር አልነበራትም ፡፡

5. እናኑ በመጨረሻ የተቀጠረችበት ቤት ------------ ከሁሉም የተሻለ ነው ፡፡











## ንባብ

### ቅድመ ንባብ

ሀ . በቤተሰገገባችሁ ውስጥ የስራ ክፍፍል አለ? የእናንተ የስራ ድርሻ ምንድን ነው?

ለ .  ስዕሉን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለ ምን እንደሚገልጽ ገምቱ?

ሐ . ርዕሱ እና ስዕሉ ምን ግንኙነት አላቸው ብላችሁ ትገምታላችሁ?

### የስራ ክፍፍል

ወ/ሮ ምንታምርና አቶ ተሰማ አራት ልጆች ያሏቸው ባልና ሚስት ናቸው፡፡ የልጆቻቸው ስም አገርነሽ፣ ካሳሁን፣ማስተዋል እና መልኬ ይባላሉ፡፡ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ይህ ስራ የወንድ ነው ይህኛው ደግሞ የሴት ነው የሚባል የስራ አይነት የለም የቤተሰቡ አባላት ስራቸውን የሚያከናውኑት በተራ ነው እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ነገ ምን እንደሚያከናውኑ በዝርዝር ይፅፋል ከመፃፉ በፊት የቤተሰቡ አባላት ምን መስራት እንደሚፈልጉ ፈቃዳቸው

ይጠየቃል፡፡ ፈቃደኛ ሆነው ካልተገኙ ግን የስራ ክፍፍሉ በምደባ ይሆናል፡፡ የስራ ድልድሉ አቅምና እድሜን ያገናዘበ ይሆናል፡፡ እናትና አባት ከበድ ያለውን ስራ ይመደባሉ፡፡ ልጆች ደግሞ አቅማቸውን ባገናዘበ መልኩ ይመደባሉ፡፡

የቤተሰቡን የአንድ ቀን የስራ ውሎ ምን እንደሚመስል እንመልከት፡፡ ዛሬ ቁርስ ማዘጋጀት የትልቁ ልጅ የካሳሁን ተራ ነው፡፡ ካሳሁን ከእንቅልፉ በጠዋት ተነስቶ ለፓስታ መቀቀያ የሚሆን ውሃ በመጣድ ፓስታውን መጨመርና ሽንኩርት ከትፎ በዘይትና በቲማቲም ከአቁላላ በኂላ የተቀቀለውን ፓስታና የተቁላላውን ማባያ በቤተሰቡ ቁጥር በስድስት ሳህኖች ከሹካና ከማንኪያ ጋር አቀረበ፡፡

ትንሹልጅ መልኬ ደግሞ በሌላ ምድጃ ሻይ በማፍላት ስድስት ብርጭቆ ላይ ቀዳ፡፡ እናትና አባት ቅርስና ምሳ የልጆቹ ተራ መሆኑን ስለሚያውቁ ከመኝታቸው ተነስተው እጃቸወን ታጥበው የተዘጋጀውን ቁርስ ተመገቡ፡፡

በዚያም ቤት የሚቆዩት ልጆች ማታ በተዘጋጀው ዝርዝር መሰረት ስራቸውን እንዲያከናውኑ ነግረው ወደ ስራ ሄዱ፡፡

ሀ/ ካሳሁን ቁርስ ሲያቀርብ ሻይ የቀዳው ማነው?

ለ/ ሁሉም ቤተሰቦች የስራ ድርሻቸውን ያከናውናሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

መልኬና ማስተዋል የዚህ ሳምንት ፈረቃቸው ከሰዓት በኂላ ነው፡፡ ስከዚህ ቁርስ የተበላበትን እቃ በማንሳት ጠረጴዛውን አፀዱ፡፡ የቆሸሹትንም እቃዎች አጠቡ ከዚያም የቤት ስራቸውን ሰርተው ሲጨርሱ ለመጫወት ወደ ውጪ ወጡ፡፡ የካሳሁን ታናሽ አገርነሽም በተመደበላት የስራ ድርሻ መሰረት የሁሉንም መኝታ አልጋዎች አነጠፈች፡፡ በተጨማሪም የምሳ ወጥ ሰራችች፡፡ በኂላም የቤት ስራ ሰርታ ስትጨርስ ትላንት የተማሩትን የትምህርት አይነቶች ሁሉንም ከለሰች፡፡ አገርነሽ የት/ት ሰዓት ሲደርስ ማስተዋልና መልኬን ጠራቻቸውና የመጫወቻ እቃዎቻቸውን እንዲያስቀምጡ ነገረቻቸውና ምሳቸውን በልተው የት/ት መሳሪያቸውን ይዘው ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ፡፡ በምሳ ሰዓት ወደ ቤት ቀድሞ የደረሰው አባትየው ነው፡፡ ቡና ለማፍላት አሰበና ልብሱን ቀይሮ ማብሰያ ክፍል ገባና ቡናውን ቆልቶ ጀበና ጥዶ ተመልሶ ሳሎን አረፍ አለ፡፡ ከባለቤቱ በመቀጠል እናትየው መጣችና ለባለቤቷ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኂላ ወደ እቃ ቤትገብታ ቡናውን ወቀጠች አቶ ተሰማ ምግብ እንብላ በማለት ሳህንና የሚጠጣ ውሃ አቀረበ፡፡ ባለቤቱ ደግሞ ወጥና እንጀራ አቀረበች ባልና ሚስቱ ለመመገብ ሳሎን እንደተቀመጡ ልጃቸው ካሳሁን መጣ ቦርሳውን አስቀመጠ ልብሱን ቀይሮ እጁን ታጥቦ አብሮ ምሳውን ተመገቡ፡፡ ከዚያም ካሳሁን አባትየው ለጣደው ጀበና በቂ የቡና ዱቄት በመጨመር ቡናው ሲፈላ ቀድቶ ለወላጆቹ ሰጣቸው ቡናውን ጠጡ

በመጨረሻም ልብሳቸውን ቀይረው የእራት ተረኞች መሆናቸውን ተናግረው ወደ ስራቸው ገቡ፡፡

***ሀ. ‹‹የስራ ክፍፍል›› የሚለው ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ትክክል ከሰልሆ ‹‹ሀሰት›› በማለት መልስ/ሺ/***

1. በቤተሰቡ የስራ ክፍፍል ይህ የወንድ ይህ ደግሞ የሴት ስራ ነው ተብሎ ይከፋፈላል፡፡
2. በእለቱ የመልኬ የስራ ድርሻ ወጥ መስራት ነው፡፡
3. የስራ ድልድሉ አቅምና እድሜን ያገናዘበ ነው፡፡
4. በምሳ ሰዓት ወደ ቤት ቀድማ የደረሰችው እናትየው ነች፡፡
5. ለመጫወት ወደ ውጭ የወጡት መልኬና ማስተዋል ናቸው፡፡

***ለ . ‹‹የስራ ክፍፍል›› የሚለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ መልስ /ሺ/***

1.ቤት ውስጥ ቤተሰብን ስራ በአቅም ማገዝ በትምህርታችን ጎበዝእንዳንሆን ያደርጋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

2.በምሳ ሠዓት ከእናትና ከአባቱ ቀጥሎ የደረሰውና ቡናው ሲፈላ የቀዳው ማነው ?

3. የቤተሰቡ አባል ነገ የሚሰሩትን ስራ ለምን በዝርዝር ይፅፋሉ?

4. በዚህ ቤተሰብ ውስጥ የመከባበርና የመተሳሰብ ሁኔታ ምን ይመስላል ?

5. ከዚህ ምንባብ ምን ትማራላችሁ?

***ሐ. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን በ‹‹ሀ›› ክፍል የተዘረዘሩትን ቃላትና ሀረጋት ከ ‹‹ለ›› ክፍል ተመሳሳየቸውን አዛምድ/ጂ ፡፡***

| ‹‹ ሀ ›› | ‹‹ ለ ›› |
|---|---|
| 1. ቀይረው | ሀ/ ማሰናዳት |
| 2. ከለሰች | ለ/ ሲያተናቅቁ |
| 3. ሲጨርሱ | ሐ/ ክፍፍል |
| 4. ማዘጋጀት | መ/ ለውጠው |
| 5. ድልድል | ሠ/ ደገመች |

**መ .በምንባቡ መሰረት በሰንጠረዥ የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በአረፍተ ነገር ውስጥ በመጠቀም ክፍት ቦታውን አሟሉ**

| | | |
|---|---|---|
| ባገናዘበ | ቀይሮ | መሳሪያዎቻቸው |
| መቀቀያ | የሚያከናውኑት | |

1. ካሳሁን ከእንቅልፉ በጧት ተነስቶ ለፓስታ ________________ ውሃ ጣደ፡፡
2. አባትየው ቡና ለማፍላት አሰበና ልብሱን____________________ማብሰያ ገባ፡፡
3. መልኬና ማተዋል ምሳቸውን በልተው የትምህርት____________ይዘው ት/ቤት ሄዱ፡፡
4. የቤተሰቡ አባላት ስራቸውን___________________ ነው፡፡
5. ልጆች ደግሞ አቅማቸውን ___________________ መልኩ ይመደባሉ፡፡

**ሠ . ‹‹የቤተሰብ የስራ ክፍፍል›› በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት ቅደም ተከተሉን በማስተካከል አንድ አንቀጽ ለማድረግ ቁጥሩን በመምረጥ ፃፍ/ፊ/ ::**

1. ሽንኩርት ከትፎ በዘይትና ቲማቲም ከአበሰለና ከአቁላላ በኂላ
2. በቤተሰቡ ቁጥር በስድስት ሳህኖች ከሹካና ማንኪያ ጋር አቀረበ፡፡
3. ዛሬ ቁርስ ማዘጋጀት የትልቁ ልጅ የካሳሁን ተራ ነው፡፡
4. የተቀቀለውን ፓስታና የተቁላላውን ማባያ
5. ካሳሁን ከእንቅልፉ በጠዋት ተነስቶ ለፓስታ መቀቀያ ውሃ በመጣድ ፓስታውን ጨመረና

ሀ/ 5፣4፣1፣3፣2　　　　ሐ/3፣5፣1፣4፣2

ለ/ 1፣5፣3፣2፣4　　　　መ/ 3፣1፣2፣5፣4

## አባሪ መ

## በሶስት አራሚዎች የታረመ የተማሪዎች የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት

## የቁጥጥር ቡድን

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 51 | 14 | 15 | 10 | 12 | 51 | 56 | 15 | 15 | 12 | 14 | 56 |
| 86 | 24 | 30 | 16 | 16 | 86 | 94 | 29 | 27 | 20 | 18 | 94 |
| 59 | 18 | 15 | 12 | 14 | 59 | 67 | 18 | 21 | 14 | 14 | 67 |
| 65 | 18 | 21 | 14 | 12 | 65 | 75 | 20 | 23 | 16 | 16 | 75 |
| 48 | 14 | 12 | 10 | 12 | 48 | 51 | 17 | 12 | 10 | 12 | 51 |
| 49 | 18 | 17 | 8 | 6 | 49 | 75 | 20 | 21 | 18 | 16 | 75 |
| 58 | 18 | 20 | 10 | 10 | 58 | 58 | 15 | 17 | 12 | 14 | 58 |
| 67 | 18 | 23 | 12 | 14 | 67 | 71 | 18 | 23 | 14 | 16 | 71 |
| 53 | 15 | 18 | 10 | 10 | 53 | 67 | 20 | 17 | 16 | 14 | 67 |
| 63 | 15 | 18 | 14 | 16 | 63 | 75 | 21 | 20 | 18 | 16 | 75 |
| 40 | 12 | 11 | 8 | 10 | 40 | 48 | 14 | 12 | 12 | 10 | 48 |
| 65 | 15 | 20 | 14 | 14 | 65 | 77 | 20 | 23 | 16 | 18 | 77 |
| 59 | 16 | 17 | 14 | 12 | 59 | 60 | 17 | 15 | 14 | 14 | 60 |
| 57 | 18 | 11 | 18 | 10 | 57 | 51 | 15 | 12 | 10 | 14 | 51 |
| 56 | 17 | 15 | 10 | 14 | 56 | 63 | 17 | 12 | 16 | 18 | 63 |
| 44 | 8 | 12 | 10 | 14 | 44 | 54 | 18 | 15 | 12 | 14 | 54 |
| 51 | 15 | 14 | 8 | 12 | 51 | 62 | 15 | 15 | 16 | 16 | 62 |
| 54 | 18 | 12 | 14 | 10 | 54 | 73 | 21 | 18 | 18 | 16 | 73 |
| 61 | 14 | 17 | 16 | 14 | 61 | 65 | 18 | 17 | 14 | 16 | 65 |
| 54 | 11 | 18 | 10 | 15 | 54 | 60 | 15 | 17 | 14 | 14 | 60 |
| 67 | 17 | 18 | 15 | 17 | 67 | 71 | 17 | 20 | 16 | 18 | 71 |
| 58 | 18 | 14 | 12 | 14 | 58 | 64 | 17 | 17 | 14 | 16 | 64 |
| 50 | 12 | 11 | 12 | 15 | 50 | 57 | 15 | 14 | 16 | 12 | 57 |
| 47 | 11 | 18 | 8 | 10 | 47 | 43 | 14 | 11 | 8 | 10 | 43 |
| 83 | 26 | 23 | 16 | 18 | 83 | 91 | 26 | 27 | 20 | 18 | 91 |
| 52 | 14 | 18 | 6 | 14 | 52 | 77 | 23 | 24 | 16 | 14 | 77 |
| 59 | 17 | 14 | 12 | 16 | 59 | 65 | 17 | 18 | 12 | 18 | 65 |
| 55 | 16 | 15 | 12 | 12 | 55 | 56 | 17 | 15 | 14 | 10 | 56 |
| 63 | 18 | 21 | 10 | 14 | 63 | 62 | 15 | 17 | 14 | 16 | 62 |
| 82 | 23 | 23 | 18 | 18 | 82 | 89 | 27 | 24 | 18 | 20 | 89 |
| 55 | 14 | 17 | 10 | 14 | 55 | 68 | 15 | 21 | 14 | 18 | 68 |
| 42 | 11 | 9 | 12 | 10 | 42 | 43 | 12 | 11 | 12 | 8 | 43 |
| 43 | 12 | 9 | 12 | 10 | 43 | 48 | 14 | 14 | 10 | 10 | 48 |
| 55 | 14 | 17 | 10 | 14 | 55 | 59 | 17 | 12 | 16 | 14 | 59 |
| 79 | 20 | 23 | 18 | 18 | 79 | 89 | 27 | 26 | 18 | 18 | 89 |
| 57 | 16 | 15 | 16 | 10 | 57 | 61 | 14 | 17 | 14 | 16 | 61 |
| 56 | 18 | 14 | 14 | 10 | 56 | 63 | 20 | 17 | 12 | 14 | 63 |
| 70 | 20 | 20 | 16 | 14 | 70 | 76 | 21 | 23 | 16 | 16 | 76 |
| 54 | 17 | 15 | 12 | 10 | 54 | 59 | 18 | 17 | 10 | 14 | 59 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 76 | 22 | 20 | 16 | 18 | 76 | 91 | 27 | 26 | 18 | 20 | 91 |
| 58 | 15 | 18 | 12 | 13 | 58 | 63 | 18 | 15 | 16 | 14 | 63 |
| 67 | 20 | 22 | 14 | 11 | 67 | 74 | 20 | 20 | 18 | 16 | 74 |
| 67 | 17 | 20 | 14 | 16 | 67 | 76 | 24 | 18 | 16 | 18 | 76 |
| 66 | 20 | 18 | 12 | 16 | 66 | 73 | 21 | 20 | 18 | 14 | 73 |
| 62 | 20 | 15 | 14 | 13 | 62 | 66 | 17 | 17 | 14 | 18 | 66 |
| 55 | 11 | 17 | 15 | 12 | 55 | 61 | 18 | 15 | 14 | 14 | 61 |
| 67 | 20 | 20 | 13 | 14 | 67 | 73 | 21 | 20 | 14 | 18 | 73 |
| 64 | 20 | 17 | 13 | 14 | 64 | 70 | 20 | 20 | 16 | 14 | 70 |
| | | | | | | | | | | | |
| 2849 | 795 | 817 | 602 | 632 | 2849 | 3190 | 895 | 868 | 706 | 726 | 3190 |

## አባሪ ሠ

## በሶስት አራሚዎች የታረመ የተማሪዎች የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት

## የሙከራ ቡድን

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 61 | 18 | 19 | 12 | 12 | 61 | 89 | 26 | 29 | 16 | 18 | 89 |
| 45 | 15 | 10 | 10 | 10 | 45 | 85 | 24 | 23 | 14 | 14 | 85 |
| 63 | 18 | 21 | 12 | 12 | 63 | 84 | 26 | 26 | 16 | 16 | 84 |
| 60 | 19 | 15 | 12 | 14 | 60 | 87 | 27 | 26 | 18 | 16 | 87 |
| 67 | 17 | 18 | 16 | 16 | 67 | 81 | 23 | 24 | 16 | 18 | 81 |
| 57 | 18 | 15 | 10 | 14 | 57 | 89 | 26 | 27 | 18 | 18 | 89 |
| 58 | 15 | 21 | 10 | 12 | 58 | 73 | 21 | 23 | 16 | 14 | 73 |
| 60 | 16 | 20 | 12 | 12 | 60 | 84 | 26 | 24 | 16 | 18 | 84 |
| 61 | 15 | 18 | 12 | 16 | 61 | 81 | 23 | 24 | 16 | 18 | 81 |
| 51 | 14 | 15 | 10 | 12 | 51 | 71 | 20 | 23 | 14 | 14 | 71 |
| 63 | 18 | 21 | 12 | 12 | 63 | 77 | 20 | 23 | 18 | 16 | 77 |
| 63 | 17 | 18 | 14 | 14 | 63 | 73 | 20 | 23 | 14 | 16 | 73 |
| 61 | 15 | 15 | 15 | 16 | 61 | 91 | 26 | 27 | 18 | 20 | 91 |
| 60 | 17 | 21 | 10 | 12 | 60 | 85 | 23 | 26 | 18 | 18 | 85 |
| 64 | 18 | 20 | 14 | 12 | 64 | 81 | 21 | 26 | 16 | 18 | 81 |
| 50 | 15 | 15 | 10 | 10 | 50 | 71 | 20 | 23 | 14 | 14 | 71 |
| 63 | 17 | 18 | 14 | 14 | 63 | 77 | 21 | 24 | 16 | 16 | 77 |
| 57 | 16 | 15 | 12 | 14 | 57 | 90 | 27 | 29 | 16 | 18 | 90 |
| 62 | 18 | 20 | 16 | 18 | 62 | 87 | 26 | 27 | 16 | 18 | 87 |
| 60 | 17 | 18 | 13 | 12 | 60 | 84 | 23 | 27 | 16 | 18 | 84 |
| 64 | 18 | 20 | 12 | 14 | 64 | 81 | 23 | 26 | 16 | 16 | 81 |
| 54 | 15 | 15 | 12 | 12 | 54 | 79 | 20 | 23 | 16 | 20 | 79 |
| 58 | 18 | 15 | 12 | 13 | 58 | 79 | 23 | 26 | 12 | 18 | 79 |
| 54 | 15 | 15 | 10 | 14 | 54 | 91 | 26 | 27 | 20 | 18 | 91 |
| 61 | 17 | 18 | 14 | 12 | 61 | 67 | 18 | 23 | 14 | 12 | 67 |
| 63 | 15 | 18 | 14 | 16 | 63 | 71 | 17 | 24 | 16 | 14 | 71 |
| 48 | 12 | 14 | 10 | 12 | 48 | 76 | 20 | 24 | 16 | 16 | 76 |
| 59 | 16 | 18 | 12 | 13 | 59 | 68 | 18 | 20 | 16 | 14 | 68 |
| 55 | 15 | 18 | 10 | 12 | 55 | 85 | 23 | 24 | 18 | 20 | 85 |
| 60 | 18 | 17 | 13 | 12 | 60 | 76 | 20 | 26 | 14 | 16 | 76 |
| 64 | 18 | 20 | 12 | 14 | 64 | 89 | 26 | 27 | 18 | 18 | 89 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 59 | 17 | 15 | 13 | 14 | 59 | 87 | 24 | 27 | 18 | 18 | 87 |
| 58 | 15 | 17 | 12 | 14 | 58 | 80 | 24 | 26 | 14 | 16 | 80 |
| 59 | 18 | 16 | 12 | 13 | 59 | 94 | 27 | 29 | 20 | 18 | 94 |
| 61 | 17 | 18 | 12 | 14 | 61 | 87 | 26 | 27 | 18 | 16 | 87 |
| 58 | 17 | 15 | 12 | 14 | 58 | 84 | 23 | 27 | 16 | 18 | 84 |
| 66 | 17 | 20 | 14 | 14 | 66 | 88 | 27 | 27 | 16 | 18 | 88 |
| 64 | 15 | 18 | 16 | 15 | 64 | 90 | 27 | 29 | 18 | 16 | 90 |
| 63 | 15 | 18 | 14 | 16 | 63 | 81 | 26 | 23 | 16 | 16 | 81 |
| 63 | 18 | 15 | 15 | 15 | 63 | 99 | 29 | 30 | 20 | 20 | 99 |
| 58 | 18 | 18 | 10 | 12 | 58 | 84 | 26 | 26 | 14 | 18 | 84 |
| 61 | 15 | 15 | 16 | 15 | 61 | 77 | 20 | 23 | 16 | 18 | 77 |
| 59 | 15 | 18 | 12 | 14 | 59 | 80 | 20 | 26 | 16 | 18 | 80 |
| 55 | 14 | 17 | 10 | 14 | 55 | 77 | 20 | 23 | 16 | 18 | 77 |
| 62 | 18 | 20 | 10 | 14 | 62 | 84 | 26 | 24 | 18 | 16 | 84 |
| 64 | 18 | 18 | 14 | 14 | 64 | 81 | 23 | 24 | 18 | 16 | 81 |
| 63 | 17 | 18 | 14 | 14 | 63 | 93 | 29 | 30 | 16 | 18 | 93 |
| 56 | 15 | 16 | 13 | 12 | 56 | 87 | 26 | 27 | 16 | 18 | 87 |
| | | | | | | | | | | | |
| 2855 | 789 | 833 | 596 | 646 | 2855 | 3955 | 1126 | 1222 | 784 | 814 | 3955 |

## አባሪ ረ

## የሙከራ ቡድን በስዕላዊ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ሲማሩ







## አባሪ ሰ

**የቁጥጥር ቡድን ያለትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በክፍል ውስጥ ሲማሩ**

